29

# የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

## በውጤት ተኮር ሥርዓት

## /Balanced Score Card (BSC)/

## የተዘጋጀ የአምስት ዓመት የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ (2003 -2007 ዓ.ም)

ታህሳስ/2003

አዲስ አበባ

# ማውጫ


1. መግቢያ ....1
2. ተልዕኮ፣ ራዕይ እና ዕሴቶች ....3
3. የኤጀንሲው ጥንካሬ፣ድክመትና፣ መልካም አጋጣሚዎችና ዕሴቶች ትንተና ....4
3.1 ጠንካራ ጎኖች ....4
3.2 ደካማ ጎኖች ....5
3.3 መልካም አጋጣሚዎች ....6
3.4 ስጋቶች( Threats) ....7
4. አስቻዮችና ፈታኝ ሁኔታዎች ....8
4.1 አስቻዮች (Enablers) ....8
4.2 ፈታኝ ሁኔታዎች (Challenges) ....9
5 የተቋሙ ተገልጋዮች /ባለድርሻ/ አካላት ትንተና ....10
6 የኤጀንሲው ተልዕኮ ከአገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር ያለው ትስስርና ትንተና ....24
6.1 የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጉዳዮች ....24
6.2 የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ....24
6.3 የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ....25
6.4 የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራም ....26
6.5 የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነታ ፖሊሲና ስትራቴጂ ....26
* 7 የተቋሙ ስትራቴጂአዊ የትኩረት መስኮችና ውጤቶች ....30
7.1 የትኩረት አቅጣጫ 1 የስታቲስቲክስ ሕጉን ሥራ ላይ ማዋል (መተግበር) ....30
7.2 የትኩረት አቅጣጫ 2 የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ስልቶችን(መርሆዎችን) ማዘጋጀትና መተግበር ....31
7.3 የትኩረት አቅጣጫ 3 ስታቲስቲክስን የማስተዋወቅና ጥቅሙን የማስገንዘብ ሥራ በስፋው መሥራት፣ ....32
7.4 የትኩረት አቅጣጫ 4 የአሠራር ሥልቶችን (ሜቶዶሎጂ) ማሻሻልና ዘመናዊ ማድረግ ....33
7.5 የኤጀንሲው ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች፣መግለጫዎችና ውጤቶች ....35
8. ዕይታዎች (Perspectives) ....36

# ክፍል 9


9. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ስትራቴጂያዊ ግቦች ....................................38
10. የማ.ስ.ኤ. ስትራቴጂያዊ ግቦች መግለጫ....................................30
11. የኤጀንሲው ስትራቴጂ ማፕ ....................................46
12. የማ.ስ.ኤ. የትኩረት መስክ መለኪያዎች መግለጫ ....................................47
13. የማ.ስ.ኤ. ስትራቴጂያዊ ዒላማዎች መግለጫ....................................55
14. ለውይይት የቀረበ (Brainstorming) ስትራቴጂክ እርምጃዎች ....................................59
15. ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች....................................61

# ክፍል 1

## 1. መግቢያ

የአንድን አገር የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የስነሕዝብ ሁኔታን የሚያንፀባርቁ አጠቃላይ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ድህነትን ለመቅረፍ የሚቀረጹ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ለማዘጋጀትና በተግባር ላይ ሲውሉም ያስገኙትን ውጤት ለመገምገም፣ ለመከታተልና የተለያዩ ጥናቶችን ለማካሄድ አስፈላጊና መሠረታዊ ግብዓት መሆናቸው ይታወቃል፡፡

አገራችን ከፌደራል የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጋር ውጤታማ የሆኑ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችን በማውጣትና በመተግበር ለተከታታይ ዓመታት በአማካይ 11 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት በማሳየት እስከ አሁን ድረስ በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ለውጥና ድል አስመዝግባለች፡፡ በመንግስት በኩል የተጀመሩ የድኀነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች፣ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች፣ ሌሎች ብሔራዊና ክልላዊ የሴክተር ልማት ዕቅዶች ላይ ጠንካራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋት በአገሪቱ ልማት ላይ እያመጡ ያለውን ለውጥ በተጨባጭ ስታቲስቲካዊ መረጃ መለካት ያስፈልጋል፡፡

ለየዘርፉ ከሚዘጋጀው የልማት ፖሊሲ በተጨማሪ ሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች የመሠረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ ተግባራዊ እንዲያደርጉና ለዚሁም መሠረቱ የውጤት ተኮር ምዘና ሥርአት በመሆኑ ለሁለንተናዊ የአገሪቱ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡

መንግስት የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ስርዓቱን በመደገፍ አገራዊ ልማቱንና የመልካም አስተዳደር ውጤቶችን ለመለካት ለክትትልና ግምገማ ስርዓቱ ከፍተኛ ድጋፍ የሚሰጡትን የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚዳስሱ ጥናቶችና ቆጠራዎችን ለማካሄድ የሚረዳ በአንፃራዊነት በየጊዜው እያደገ የሄደ በጀት እየመደበ ይገኛል፡፡ መንግሥት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እያካሄደ ያለውን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ነክ መረጃዎች የማመንጨት ተግባርና ጥረት እያጠናከረ ከመሆኑም በላይ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ስርዓቱን እንዲያስተባብርና ለልማት ዕቅዱ ጠቃሚ መረጃዎችን እንዲያቀርብና ለክትትልና ግምገማ ተግባሩም ማዕከል እንዲሆን እያደረገው ይገኛል፡፡

የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ስርዓቱ መሻሻል ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለክትትልና ለግምገማ ወይም ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን እንደገና ለማየት ብቻ ሳይሆን ለአጠቃላይ ኅብረተሰቡ ለውሳኔ የሚረዱ መረጃዎችን በማመንጨትም ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ይህም የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ስርዓቱ ለሁሉም ዜጋ ተደራሽ አስተማማኝ የስታቲስቲክስ መረጃ ከማቅረብ በተጓዳኝ ለማኔጅመንት የመረጃ ስርዓት የተሟላ ግብዓት በመሆን ለከፍተኛ የመንግሥት አካላትና ለእያንዳንዱ ዜጋም ተጠቃሚነቱን ከፍ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ወጥ የሆነ አፈሻያል

የስታቲስቲክስ ስርዓት በመዘርጋት ያለውን የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችና ለውጦች መደገፍ ብሎም አለማቀፋዊ ተነፃፃሪ በመሆን ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ እንዲሆንም መደረግ አለበት፡፡ የዚህ ዓይነት ሥርዓት ከተዘረጋ ደግሞ ፖሊሲዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ስትራቴጂዎችን ከትክክለኛ መረጃ በመነሣት ተግባራዊነታቸውን ለመከታተል ያግዛል፡፡

አገራችን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ዲሞግራፊያዊ (የስነ-ሕዝብ) ሁኔታዎችን የሚዳስሱ የናሙና ጥናቶችንና ቆጠራዎች በማቀድና በማካሄድ የረጅም ጊዜ ልምድ ያላት አገር ናት፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ባለፉት አምስት ዓመታት እነዚህን ጥናቶችና ቆጠራዎች ለማካሄድ በመንግስት ከፍተኛ በጀት ተመድቧል፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ብሔራዊ የተቀናጀ የቤተሰብ ሰርቬይ ፕሮግራምንና የሕዝብና ቤት ቆጠራ በተሳካ መንገድ ለማካሄድ አስችሎታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ስርዓቱን በሁሉም ዘንድ ለማስተዋወቅ የመካከለኛ ጊዜ የስታቲስቲክስ ፕሮግራም በማዘጋጀት ከ1997-2001 ተግባራዊ አድርጓል፡፡

አዲስ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ ከ2002 - 2006 ያሉትን ዓመታት የሚሸፍን ዕቅድ በቅርብ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ዕቅዱም ካለፈው የመካከለኛ ዘመን የስታቲስቲክስ ፕሮግራም በቅርፅ፣ በይዘትና በሽፋን የተለየ ነው፡፡ አዲሱ ስትራቴጂ አጠቃላይ የስታቲስቲክስ አቅሙን ለማጎልበት የሚበጅ ሲሆን፣ ስነዱ ስትራቴጂውን ተግባራዊ ለማድረግ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን የፈተሸና የተለያዩ የስትራቴጂ ጭብጦችንና የሥራ ቅደም ተከተል ያለውና ከ2002 በጀት ዓመት ጀምሮ በመተግበር ላይ የሚገኝ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ መንግስት የቀጣዩን አምስት ዓመታት (2003-2007) የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ያዘጋጀ ሲሆን ከዚህ ጋር የተጣጣመ አዲስ ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ልማት ዕቅድና የአሠራር ስልት በመከለስና በማዘጋጀት የሥራ መርሃ-ግብርና የስታቲስቲክስ አቅም ግንባታ በአገር አቀፍ ደረጃ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ከ2003-2007 የሚተገበርና በክንዋኔ ሂደት ላይ ያለውን የብሔራዊ የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ መሠረት አድርጎ የተሻለ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ልማት ዕቅድና መርሃ-ግብር ተዘጋጅቷል፡፡

በአዲሱ ስትራቴጂ የስታቲስቲክስ የልማት ስትራቴጂና ዕቅድ በርካታ የለውጥና የማሻሻያ ሥራዎች የሚሠሩ ሲሆን በዋነኛነት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲን የመተግበርና የማስተባበር ኃላፊነት እንዲሁም ሙያዊ ስነ-ምግባር የተላበሰ ባለሙያ የማፍራት፣ የጥራት ደረጃና ምደባን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል አቅም የሚፈጥር ነው፡፡ በዚህ የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ የቤተሰብ ሰርቬይና የኢኮኖሚ ጥናቶች አሰራር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚሻሻልና እንደሚለወጥ ይጠበቃል፡፡ እንዲሁም ሰፊና አጠቃላይ የሆነ የአዳዲስ ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚያስችል የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ በመሆኑ የሚካሄዱ

ጥናቶችና ቆጠራዎች እንዲሁም ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎች ጥራትና ወቅታዊነት በዕቅድ ዘመኑ ከፍተኛ መሻሻል ይደረግባቸዋል::

በአሁኑ ወቅት ደግሞ የውጤት ተኮር ሥርዓት /BSC/ ሰነድን ለማዘጋጀት እንዲቻል የመልካም አጋጣሚና ስጋት ትንተና (SWOT) ቀደም ሲል የተዘጋጀውን እንደገና በመፈተሽ እንዲሁም የመሠረታዊ የሥራ ሂደት /BPR/ የለውጥና የማሻሻያ ሥራዎችን ይበልጥ ለማጠናከርና ተጨባጭ ለማድረግ የኤጀንሲውን ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴቶችና የትኩረት መስኮችን በመቀመርና በተቋም ደረጃ ከቡድንና ከግለሰብ ፈጻሚ የሚጠበቁ ውጤቶችን ለመለካት፣ ለመገምገምና ለመከታተል የሚያስችል፣ ይህ በውጤት ተኮር ስርዓት ላይ የተመሠረተ የአምስት ዓመት የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂያዊ ዕቅድ ተዘጋጅቷል:: በዚህ ሰነድ ዝግጅት ላይ የኤጀንሲው ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ተለይተው በአኳያው ስትራቴጂያዊ ግቦች የተቀመጡ ሲሆን የሥራ እንቅስቃሴዎችን ማለትም የጥናቶችና የቆጠራዎች መርሃ-ግብር፣ በጀትና የሚጠበቁ ውጤቶችና የተፈጻሚነታቸውን ደረጃ ለመገምገምና ለመከታተል የሚያስችል ስልቶችም በዝርዝር ተቀርጸዋል::

# ክፍል 2

## 2. የኤጀንሲው ተልዕኮ፣ ራዕይና ዕሴቶች

### 2.1 ተልዕኮ

ለልማት ፖሊሲዎች ቀረፃ፣ ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለጥናትና ምርምር፣ እንዲሁም ለክትትልና ግምገማ ግብዓት የሚሆን ወቅታዊ፣ የጥራት ደረጃውን የጠበቀና የተቀናጀ የኦፊሺያል ስታቲስቲክስ መረጃ ማመንጨት፣ ማሠራጨትና የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን ማስተባበር፣

### 2.2 ራዕይ

በ2012 ዓ.ም. በስታቲስቲክስ መረጃ ጥራትና አቅርቦት በአፍሪቃ በሞዴልነት የሚጠቀስ መሪ ተቋም መሆን፣

### 2.3 ዕሴቶች

- ወቅታዊና ጥራት ያለው የስታቲስቲክስ መረጃ እናቀርባለን፣
- የተቀናጀና ዘመናዊ አሰራር እናሰፍናለን፣
- ለሰዉ ሀብት ልማት ትኩረት እንሰጣለን፣
- የቡድን ስራ እናሰፍናለን፣
- የተገልጋዮችን ፍላጎት ያገናዘበ የስታትስቲካዊ ጥናቶች እናካሂዳለን፣

- ለሙያ ክብርና ፍቅር መስጠት፣
- ለመረጃ ሰጭዎቻችን ተገቢዉን አክብሮት መስጠት፣
- ግልፅነት ፣ ተጠያቂነትና አሳታፊነት መርሆችን ነው፣
- ህግና ደንብ በአግባቡ በመተግበር ለዉጤት እንተጋለን፣
- ባስቸጋሪ ሁኔታ ዉስጥ ስራ ተባብረን እንሰራለን፣
- ከልማት አጋሮች ጋር መልካም ግንኙነት እንፈጥራለን፣
- የመማርና የመለወጥ ተነሳሽነትን መኖር፣
- ለዓለም አቀፍ ዕውቅናና ተወዳዳሪነት ትኩረት እንሰጣለን፣
- ጥሩ የሥራ ግንኙነት ለውጤታችን የጎላ ሚና እንደሚኖረው እናምናለን፣

# ክፍል 3

## 3. የኤጀንሲው ጥንካሬ፣ ድክመት መልካም አጋጣሚዎችና ስጋቶች ትንተና (ጥ.ድ.መ.ስ)

የጥንካሬዎች፣ ድክመቶች፣ መልካም አጋጣሚዎችና ሥጋቶች ትንተና የአንድን ተቋም ውስጣዊ ሁኔታ እና ከተቋሙ የሥራ ዕንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት የሚኖራቸው ውጫዊ ሁኔታዎችን የሚዳስስ ትንተና ከመሆኑም በተጨማሪ የተቋሙ ዕቅድ ሲቀረፅ መሰረታዊና ቁልፍ የሆኑ ጉዳዮች ትኩረት እንዲሰጣቸው ያደርጋል፡፡ ትንተናው ሲከናወን ጥንካሬና ድክመት የተቋሙን ውስጣዊ ሁኔታ የሚዳስሱ ሲሆን መልካም አጋጣሚና ስጋት ተቋሙ ከውጫዊው ሁኔታዎች (External factors) የሚያጋጥሙትን ምቹ ሁኔታዎችና ተጽዕኖዎችን ይዳስሳል፡፡

### 3.1 የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ጥንካሬዎች (ጠንካራ ጎኖች)

- የሪፎርም ሥራዎችንና የመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ የመተግበር፣ የማሻሻል፣ የመገምገምና የመከታተል ተነሳሽነትና ብቃት መኖሩ፣
- ለረጅም ዘመናት ጥራት ያለው መረጃ በአገሪቱ ማቅረብ መቻሉ፣
- የሕትመት ውጤቶች ውስጥ Metadata(ስለጥናት መግለጫዎች) እና Sampling error (በናሙና መረጣ የሚከሰቱ ስህተቶች) መካተታቸው፣
- የሰለጠኑ ስታቲስቲሽያኖች፣ ፕሮግራመሮችና ሌሎች ባለሙያዎች ስብጥርና ብዛት እያደገ መምጣቱ፣
- ኤጀንሲው የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም ግንባታና ዕቅድ ላይ በአግባቡ የተደራጁ ከተለያዩ መ/ቤቶች የተውጣጡ የስታቲስቲክስ ቡድኖች በዕቅድ ቀረፃ እንዲሳተፍ ማድረጉ፣

- በዲስፕሊን የታነፀና በአግባቡ የሚመራ የስታቲስቲክስ ስርዓት በኤጀንሲው መኖሩ፣
- የስታቲስቲክስ ልማት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የማዘጋጀት የዳበረ ባህል መኖሩ፣
- በቅርቡ የተካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች (Scanning and Satellite Imagery) ሥራ ላይ መዋላቸው፣
- ደረጃቸውን የጠበቁ መጠይቆች የተዘጋጀላቸው በዕቅድ የሚከናወኑ ጥናቶች መከናወናቸው፣
- አገሪቱ ለምታወጣቸው የልማት ፖሊሲዎች አጋዥ የሆኑ የጥናት ውጤቶች በአብዛኛው ወቅታቸውን ጠብቀው መቅረባቸው፣
- ብቃት ያለው የመረጃ ድረ-ገፅ (Web-site) መኖሩ፣
- የልማት አጋሮች በኤጀንሲው አመኔታ እንዲኖራቸውና ተከታታይ ድጋፍ እንዲያደርጉ ከፍተኛ ጥረት መኖሩ፣
- የመረጃ አርካይቭ (ባንክ) ለሌሎች አገሮች አርአያ የሚሆን እንዲገነባ ማድረጉ፣
- ዓለም አቀፍ ደረጃን የመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት መኖሩ፣
- በሁሉም ደረጃዎች መረጃ በመሰብሰብ፣ በማቀነባበር፣ በከፍተኛ ደረጃ "ICT" እና "GIS" የመተግበር ባህል እያደገ መምጣቱ፣
- በኤጀንሲው ደረጃ እና በአገር አቀፍ ደረጃ ጥናቶችና ቆጠራዎችን የማስተባበር ልምድና አቅም መኖሩ፣
- የኮሚኒኬሽን ሥራችንን በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ጥረት እየተደረገ መሆኑ፣

## 3.2 ደካማ ጎኖች(Weaknesses)

- ስለ ስታቲስቲክስ ጥናቶችና አገልግሎቶች መረጃ ሰጪ ተኮር የሆነ የኮሙኒኬሽን ሥራ ለመሥራት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ከሚጠበቀው ሰፊ ሥራ አንፃር በቂ አለመሆኑ፣
- የስታቲስቲካል ቢዝነስ ሬጅስተር በሚገባ አለመደራጀቱ፣
- ለብሔራዊ አካውንት ስታቲስቲክስ ግብዓት የሚሆኑ የስታቲስቲክስ መረጃዎች ክፍተት መኖሩ፣
- የስታቲስቲክስ አቅርቦቱ በተለምዶ በሚሸፈኑ መስኮች ላይ በማተኮሩ ለአዳዲስ የፖሊሲ የትኩረት አቅጣጫዎች ምላሽ መስጠት አለመቻሉ፣
- ትላልቅ የናሙና ምጣኔ (Sample size) ያላቸው ጥናቶች በመረጃው ጥራት ላይ Non-sampling ስህተቶች እንዲጨምሩ ማድረጋቸው፣
- በአፊሻል ስታቲስቲክስ ጥራትና ገለልተኝነት ላይ አመኔታ ለመፍጠር እጅግ በርካታ ጥረቶች ቢደረጉም አሁንም በቂ አለመሆናቸው፣
- የተወሰኑ ጥናቶች ወቅታቸውን ጠብቀው ውጤታቸው አለመውጣቱ፣

- የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን በማስተባበር ረገድ ድክመቶች መታየታቸው፣ በተለይም የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም ውጤቶችን ከአንድ ማዕከል ወይም የመረጃ ቋት (database) ማግኘት አለመቻሉ፣
- የተወሰኑ የስታቲስቲክስ ጥናቶች በተወሰነ የጊዜ ገደብ ባለመቅረባቸው አልፎ አልፎ የመረጃ ተከታታይነት ችግር መከሰቱ፣
- በአቅም ውሱንነት የተነሳ አልፎ አልፎ የታቀዱ ጥናቶች ተግባራዊ አለመሆናቸው፣
- ደካማና ጠንካራ ፈጻሚ ሠራተኛውን በአግባቡ የሚለይ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣
- የስታቲስቲክስ ሲስተሙን ተዋንያኖች ለማሰልጠንና ለማብቃት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥራ ለማከናወን የማሰልጠኛ ችግር መኖሩ፣

## 3.3 መልካም አጋጣሚዎች (Opportunities)

- ለረጅም ዓመታት ተከታታይነት ያለውና እያደገ የሄደ የበጀ ድጋፍና የግብአት አቅርቦት መኖሩ፣
- የስታቲስቲክስ ስራን ለመደገፍ ከመንግስት ከፍተኛ የፖለቲካ ቁርጠኝነት መኖር፣
- በቅርቡ የተቋቋመዉ የስታቲስቲክስ ካዉንስል በብሄራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም ዉስጥ በተሻለ ሁኔታ ቅንጅት ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑ፣
- የፓሪስ 21 የNSDS መርሆዎች ቀርፆ ማስቀመጡ መስሪያ ቤቱ ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ልማት ስትራቴጂ ቀርጾ እንዲንቀሳቀስ አስችሎታል፣
- የበለጠ የተቀናጀ የስታቲስቲክስ ሲስተም ለመገንባት በኤጀንሲው የበላይ አመራርና በሌሎች በሚመለከታቸዉ አካላት ያለዉ ፍላጎት ለሁሉም ኦፊሻል ስታቲስቲክስ የተሻለ ቅንጅት የሚፈጥር መሆኑ፣
- በቅርቡ ተግባራዊ መሆን የጀመረዉ BPR በ NSDS ላይ የተቀመጡትን recommendations ለመፈፀም የሚያስችል መሆኑ፣
- BPR በሁሉም መረጃ በሚያመነጩ መስሪያቤቶች MIS ለማሻሻል ጥሩ እድል መፍጠሩና ይህም የብሄራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን ለማቀናጀት ጥሩ ሁኔታ መፍጠሩ፣
- በዝቅተኛ አስተዳደር እርከን (ወረዳ) ያለው የመረጃ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ የመረጃ ፍላጎትን በማሳደግ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ጥሩ አጋጣሚ መፍጠሩና በመላ ሀገሪቱ የመረጃ አሰባሰቡንና አጠቃቀሙን የሚያጠናክር መሆኑ፣
- MIS በመጠናከሩ ከየአካባቢዉ መረጃ በቀላሉ ማግኘት ማስቻሉ፣
- የፓሪስ ስምምነት (Paris declaration) መንግስትና የልማት አጋሮች የመንግስት ስትራቴጅ ላይ በማተኮር ለአቅም ግንባታ ቅድሚያ እንዲሰጡ ማገዙ፣

- ከልማት አጋሮች ጋር ያለው ግንኙነት እያደገ በመምጣቱ ከፍተኛ ዕምነት በኤጀንሲው ላይ ማሳደራቸው፣
- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ብሄራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ ለተጠቃሚዎች የተሻለ አገልግሎትና ጥራት ያለዉ መረጃ በወቅቱ እንዲሰጥ ማስቻላቸው፣
- የሥራ አካባቢን ለማሻሻል የአቅም ግንባታ ስልጠና ለመስጠት የሚያስችል ሥራዎች መኖራቸው፣
- ለዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ክትትልና ግምገማ የመረጃ ፍላጎት መጨመሩ፣

## 3.4 ስጋቶች (Threats)

- በሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶች የስታቲስቲክስ ውጤትን ተጠቅሞ በየሴክተሩ የጥልቅ ትንተና ክህሎት በጣም አናሳ መሆን፣
- የተሻሻለ ዘመናዊ ኢኮኖሚ ካለዉ የመረጃ ፍላጎት አንጻር የስታቲስቲክስ ሥራ አብሮ ለማደግ እጅግ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ መሆኑ፣
- በአንጻራዊነት ከተጠቃሚዎች ጋር ባለዉ አነስተኛ ተሳትፎና ምክክር እና ከአቅም ማነስ ምክንያት እያደገ ያለዉን የስታቲስቲክስ ፍላጎት ማሟላት አለመቻል፣
- በብሄራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተም ዉስጥ የሰለጠኑ የስታቲስቲክስና የኮምፒዩተር ባለሞያዎች የተሻለ ክፍያ ወዳላቸዉ የግል ፣ እርዳታ ሰጭና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት መሄዳቸዉ፣
- በብሄራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተም ዉስጥ እዉቀት ከተቋማት ይልቅ በግለሰቦች ደረጃ የተከማቸ መሆኑ፣
- ከአቅም ጋር ባልተገናዘበ መልኩ በየዘርፉ የተለያዩ የስታቲስቲክስ መረጃ አቅርቦት ጥያቄ በመቅረቡና ፍላጎቶችን ለመመለስ ሲባል ብዙ ሰርቬዮች እንዲካሄዱ ያለዉ ጫና ዋና ዋና መስኮች ወቅታዊነት ላይ ተፅዕኖ ማድረጉ፣
- በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከን (ወረዳ) ደረጃ መረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ መረጃ ፈላጊዎች አስተማማኝ ካልሆነ ምንጭ መረጃ መጠቀማቸው፣
- አሁን ያለው የሲቪል ሰርቪስ የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ደንብ ጥልቅ ትንተና ሊሠሩ የሚችሉ ክህሎትና ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች ለመያዝ የሚያስችል አለመሆኑ፣
- መረጃ ሰጭዎች ስለስታቲስቲክስ መረጃ ጥቅም ያላቸው ግንዛቤ አናሳ መሆኑ፣

# ክፍል 4

## 4. አስቻዮችና ፈታኝ ሁኔታዎች

### 4.1 አስቻዮች (Enablers)

- ተቋሙ ወደ መሠረታዊ ሥራ ሂደት ለውጥ (BPR) ሙሉ ትግበራ በመግባቱ የተገኙ የሥራ አፈፃፀም ማሻሻያዎችና በኤጀንሲው የታቀፉ የሥራ ሂደቶች በእነዚህ ለውጦች ውስጥ ማለፋቸው፣ እንዲሁም ኤጀንሲው በቀጣይነት ለአቅም ግንባታና ለሌሎችም መሠረታዊ ሪፎርሞች የሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ሥራን ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማከናወን ያስችላል፡፡
- በተቋሙ ያለው አንፃራዊ የተሻለ የትምህርት ዝግጅት፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል (Professional) ከገበያ የማግኘት ዕድል፣ እንዲሁም በመ/ቤቱ እየጎለበተ ካለው የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ልማት ጋር ተዳምሮ የኤጀንሲውን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት ከፍተኛ ዕድል ይፈጥራል፡፡
- መንግሥት ለሀገሪቱ የስታቲስቲክስ ሥርዓት ልማትና እድገት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱና ለተነደፈው ስትራቴጂክ ዕቅድ ተግባራዊነት የሚያስፈልገውን በጀት ከፍተኛ ድርሻ መመደቡ ለተቋሙ ተልዕኮና ራዕይ መሳካት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
- ተቋሙ ያለው አገር አቀፍ የስታቲስቲክስ ጥናቶችና ቆጠራዎችን የማካሄድና የማስተባበር ልምድና አቅም፣ ያለው የተሻለ የሥራ ድጋፍና ፋሲሊቲ፣ ስትራቴጂያዊ ዕቅዱን ከማሳካት አንፃር ከፍተኛ ዕድል ይፈጥራል፡፡
- በተቋሙ የተዘረጋው የስታቲስቲክስ ሜቶዶሎጂና ሳይንሳዊ የስታቲስቲክስ አሠራር፣ ይህንኑም አሠራር ይበልጥ ለማሻሻልና ለማጠናከር የተያዘው አቅጣጫ፣ እንዲሁም በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት ሥርዓት ለማጎልበት የተጀመረው እንቅስቃሴ የመ/ቤቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ ከማሳካት አንፃር ከፍተኛ ዕድል ይፈጥራል፡፡
- ኤጀንሲው ከልማት አጋሮች ጋር ያለው መልካም ግንኙነትና የልማት አጋሮቹም የተቋሙን ጥረት ለመደገፍ ያላቸው በጎ ፈቃድና ዝግጁነት የመ/ቤቱን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፡፡
- ሥራ ላይ የዋለው የተሻሻለው የስታቲስቲክስ አዋጅ፣ በቅርቡ የተቋቋመው አገር አቀፍ የስታቲስቲክስ ካውንስል፣ እንዲሁም በኤጀንሲው የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ጥራትና ደረጃዎች ማስተባበሪያ ሥራ ሂደት በአዲስ መልክ እንዲደራጅ መደረጉ የአገሪቱን አጠቃላይ የስታቲስቲክስ አሠራር ከማጎልበትና ከማስተባበር አንፃር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

- በኤጀንሲው የስልጠናና የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ለማከናወን ዕንቅፋት የነበሩት የዘመናዊ ቢሮና የማሰልጠኛ ቦታዎች ለመፍታት የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች የስታቲስቲክስ ሲስተሙን አቅም ለማጉልበት በር ይከፍታሉ፡፡

## 4.2 ፈታኝ ሁኔታዎች (Challenges)

- ከኤጀንሲው ውጪ ባሉ መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ባልሆኑና በግል ድርጅቶች ውስጥ ባሉ የተሻሉ ክፍያዎችና ጥቅማጥቅሞች ሳቢያ ለረጅም ጊዜ የስታቲስቲክስ አሠራር ልምድ፣ እውቀትና ክህሎት ያዳበሩ ሠራተኞች ሲለቁ መቻላቸው የመ/ቤቱን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት በሚደረገው ጥረት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ፣
- በአገሪቱ የሚገኙ የተለያዩ የስታቲስቲክስ መረጃ የሚያመነጩ ድርጅቶች የሚከተሉት የስታቲስቲክስ ሜቶዶሎጂ፣ ጽንስ ሐሳብና ትርጓሜ የተለያየ በመሆኑ የሚያመነጯቸውም የስታቲስቲክስ መረጃዎች ብዙውን ጊዜ የማይጣጣሙ ሆነው መገኘታቸው የመ/ቤቱን ተልዕኮና ራዕይ ከማሳካት አንፃር እንቅፋት የሚፈጥር መሆኑ፣
- በመስክ የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብና አደረጃጀት ሥራን በኮምፒዩተር በታገዘ አሠራር ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች አለመሟላታቸውና ይህንንም ቴክኖሎጂ ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪና የሰለጠነ የሰው ኃይል በአጭር ጊዜ ማዘጋጀት አስቸጋሪ መሆኑ በስትራተጂክ ዕቅድ አፈፃፀም እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖ ሲፈጥር መቻሉ፣
- የኤጀንሲው ዋነኛ ማንጼት ጥራት ያለው መረጃ አቅርቦት በመሆኑ በሁለተኛ ደረጃ መከናወን ያለበት የጥልቅ ትንተና ሥራ ቅድሚያ አለመስጠቱ የተቋሙ ተወዳዳሪነት ላይ የተወሰነ ችግር ያለው መሆኑ፣
- በተቋሙ ምቹ የሥራ ቦታዎች ማለትም የቢሮዎች፣ የስብሰባ አዳራሾች፣ የመጋዘኖችና የማሰልጠኛ ቦታዎች የማሟላት ሂደቱ በቅርቡ የተጀመረ በመሆኑ የራሱን ጊዜ ስለሚወስድ በታቀዱ ሥራዎች አፈጻጸም ላይ እንቅፋት የሚፈጥር መሆኑ፣
- የስታቲስቲክስ ውጤቶችና አገልግሎቶችን ከሚጠበቀው ሰፊ ሥራ ጋር በአንፃራዊነት ሲታይ በበቂ ሁኔታ የማስተዋወቅ ሥራ አለመሠራቱና የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለመረዳት የሚያስችል ተከታታይነት ያለው ጥናት አለመኖሩ የመረጃ አቅርቦትና አጠቃቀም ደረጃን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ላይ እንቅፋት የሚፈጥር መሆኑ፣
- አንዳንድ የቢዝነስ ተቋማት ተሞልቶ መላክ የሚገባውን ቅጽ ሞልተው ባለመላካቸው በመረጃ ጥራትና ሽፋን ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው፣(የቢዝነስ ሴክተሩን መረጃ በትክክል አለመስጠት)

# ክፍል 5

## የተቋሙ ተገልጋዮች /ባለድርሻ አካላት ትንተና፤

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ/ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | የተጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የማያስከትለው ተጽዕኖ | የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ተጽዕኖ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የሰብል ምርት ትንበያ | • ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>• የግብርና ሚ/ር<br>• የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>• የክልል መንግስትና ግብርና ቢሮዎች<br>• FAO<br>• WFP<br>• የግብርና ባለይዞታዎች | • ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን ስታንዳርዱን ጠብቆ በመያዝና በመስጠት መተባበር<br>• የአሠራር ሚቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና ቴክኒክ እገዛ ማድረግ<br>• ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር | • በሰብል ዘመኑ ሊገኝ የሚችለው የምርት መጠን በሰብል ዓይነት<br>• በሰብል ዘመኑ የታረሰ መሬት ስፋት በሰብል ዓይነት | የሰብል ምርት እጥረት/ትርፍን አስመልክቶ ወቅታዊና ትክክለኛ ውሳኔ እንዳይሰጥ ያደርጋል | ከፍተኛ |
| 2 | የታረሰ መሬት ስፋትና የተገኘ የምርት መጠን | ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>የግብርና ሚ/ር<br>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>የክልል ግብርና ቢሮዎች<br>FAO<br>WFP<br>የንግዱ ህብረተሰብ<br>የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>WB<br>IMF<br>የግብርና ባለይዞታዎች | • የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና ቴክኒክ እገዛ መስጠት<br>ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አመላካቾች(Indicator)ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• በዝቅተኛ አስተዳደር ደረጃ የተሟላ ከአስተዳደር መዛግበት የሚገኙ መረጃዎችን መያዝ<br>• ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር | • በሰብል ዘመኑ የተገኘ የምርት መጠን ግምት ሰብል ዓይነት<br>• በሰብል ዘመኑ የታረሰ መሬት ስፋት<br>• የሰብል ምርታማነት (Yield) | የሰብል ምርት መጠንና ምርታማነት ሁኔታ ለመገምገምና የማሻሻያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ አለመቻል፤<br>በአገሪቱ ሊታረስ ከሚችለው መሬት የታረሰውን መጠን ወይም ፐርሰንት ማወቅ አለመቻልና ትክክለኛ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ መንደፍ አለመቻል፤ | ከፍተኛ |

የተቋሙ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት.. የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ/ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | የተጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የማያስከትለው ተጽዕኖ | የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ተጽዕኖ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 3 | የመሬት አጠቃቀም መረጃ /ስታቲስቲክስ | ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>የግብርና ሚ/ር<br>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>የክልል ግብርና ቢሮዎች<br>FAO<br>የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ተመራማሪዎች<br>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን<br>የግብርና ባለይዞታዎች | ጥልቅ ትንተና በሚያስፈልጎቸው መረጃዎች ላይ የቴክኒክ እገዛ፣ በማድረግ በጋራ መሥራት፣<br>ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አመላካቾች(Indicator) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት፣<br>.የተሟላ በአስተዳደር መዛግብት የሚያዝ መረጃ ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር፣ | በጊዜያዊና ቋሚ ሰብል የተያዘ መሬት ስፋት፣<br>ግጦሽ፣በደን፣በእዳሪ መሬትና በሌሎች፣ የመሬት አጠቃቀም የተያዘ መሬት ስፋት፣<br>የአንድ ባለይዞታ አማካኝ የማሳ ስፋት፣ | .ትክክለኛ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ፣ ስትራቴጂና መርሃ-ግብር ለማዘጋጀት አስቸጋሪ ይሆናል፣<br>.ውጤታማ የሆነ የግብርና ፖሊሲ ለማዘጋጀት አያስችልም፣ | ከፍተኛ |
| 4 | የግብርና ግብአቶች አጠቃቀም ስታቲስቲክስ የሰብል ብልሽት መረጃ | ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>የግብርና ሚ/ር<br>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>የክልል ግብርና ቢሮዎች<br>FAO<br>የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>የንግዱ ህብረተሰብ<br>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን<br>የግብርና ባለይዞታዎች | የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና ቴክኒክ እገዛ መስጠት፣<br>.ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር፣<br>ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር፣ | . የማዳበሪያ፣የምርጥ ዘር፣የፀረ-ተባይ ወዘተ አጠቃቀምና ጥቅም ላይ የዋለ መጠን፣<br>.የሰብል ብልሽት መጠንና የሰብል ብልሽት ምክንያቶች፣<br>.በሬ ያላቸውና የሌላቸው አርሶ አደሮች ብዛት፣ | በአገሪቱ የሚያስፈልገውን የግብርና ግብአት መጠን ማወቅ አለመቻል፣ የሰብል ብልሽት የሚያስከትሉ በሽታዎችን አለመለየትና ትክክለኛ እርምት መውሰድ አለመቻል ፣ | ከፍተኛ |
| 5 | የቤት እንስሳትና ንብ የያዙ ቀፎዎች ስታቲስቲክስ. የእንስሳት በሽታና የክትባት ስርጭት | ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>የግብርና ሚ/ር<br>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>የክልል ግብርና ቢሮዎች<br>FAO<br>WFP<br>የንግድ ሚ/ር<br>የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>የግብርና ባለይዞታዎች | .ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት የመተባበር፣<br>.የአሠራር ሚቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና ቴክኒክ እገዛ ማድረግ፣<br>ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር፣ | .የቤት እንስሳት ብዛት በጾታ፣በዕድሜና በአገልግሎት ሁኔታ በእንስሳው ዓይነት፣<br>ንብ የያዙ ቀፎዎች ብዛት በቀፎ ዓይነት፣<br>.የወተት፣የእንቁላልና የማር ምርት መጠን፣<br>በበሽታ የተጠቁ የቤት እንስሳት ብዛት በበሽታ ዓይነት፣<br>.የተከተቡ የቤት እንስሳት ብዛት በተከተቡ በሽታ ዓይነት፣<br>.በአርብቶ አደር አካባቢ ያሉ የቤት እንስሳት ብዛትና ዓይነት፣ | የቤት እንስሳትን አስመልክቶ የሚወጡ ፖሊሲዎች ላይ ተጽዕኖ ያመጣል፣ ወደ ውጭ የሚላኩ የቤት እንስሳት ብዛት ዓይነት ለመወሰን አስቸጋሪ ይሆናል፣ የቤት እንስሳትና የማር ምርታማነትን አስመልክቶ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ስትራቴጂ ለማዘጋጀት አያስችልም፣ በሽታዎችን ለይቶ ወቅታዊ ክትባት ለመስጠትና የመድኃኒትና የሰው ኃይል አቅርቦት ለመወሰን አስቸጋሪ ይሆናል፣ | ከፍተኛ |

የተቋሙ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት... የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ / አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | የተጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የማያስከትለው ተጽዕኖ | የተገልጋዮች/ባለ ድርሻ አካላት ተጽዕኖ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | የሰብል ምርትና የእንስሳት ተዋጽኦ አጠቃቀም ስታቲስቲክስ | ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>የግብርና ሚ/ር<br>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>የክልል ግብርና ቢሮዎች<br>FAO<br>WFP<br>ተመራማሪዎች<br>የንግድ ሚ/ር<br>ብሔራዊ ባንክ<br>የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>የግብርና ባለይዞታዎች | ጥልቅ ትንተና በሚያስፈልጋቸው መረጃዎች ላይ የቴክኒክ እገዛ በማድረግ በጋራ መሥራት፣<br>ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር፣ | የሰብል ምርት አጠቃቀም /ለፍጆታ፣ለገበያ፣ለዘር፣ወዘተ የዋለ መጠን/ በሰብል ዓይነት በመቶኛ፣<br>የቤት እንስሳት ተዋጽኦና የማር ምርት አጠቃቀም በዓይነት በመቶኛ፣ | ከሰብል ምርትና ከእንስሳት የሚገኘው ገቢ በገበሬው ኑሮ ላይ ያመጣውን ለውጥ ለመገምገም አያስችልም፣<br>በዓመቱ ውስጥ ከተመረተው ምርትና ከተገኘው የእንስሳት ተዋጽኦ ለገበያ የዋለውን መጠን ለመገመትና የገቢያ ስርዓት ለመዘርጋት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ስትራቴጂ ለመንደፍ አያስችልም፣ | ከፍተኛ |
| 7 | የሰፋፊና መካከለኛ የንግድ እርሻዎች ስታቲስቲክስ | ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>የግብርና ሚ/ር<br>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>የክልል ግብርና ቢሮዎች<br>FAO<br>የንግድ እርሻ ባለቤቶች /ኢንቨስተሮች/<br>የንግድ ሚ/ር<br>ብሔራዊ ባንክ<br>የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>የኢንቬስትሜንት ጽ/ቤት<br>ተመራማሪዎች | ብቁ የሆኑ ከአስተዳደራዊ መዘግብት የሚገኙ መረጃዎችን መያዝ፣<br>ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር፣<br>የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና ቴክኒክ እገዛ መስጠት፣ | በሰፋፊና መካከለኛ የንግድ እርሻዎች የታረሰ መሬት ስፋትና የተገኘ ምርት መጠን በሰብል ዓይነት፣<br>የሰፋፊና መካከለኛ የንግድ እርሻዎች ምርታማነት (Yield) በሰብል ዓይነት፣<br>የሰፋፊና መካከለኛ የንግድ እርሻዎች የግብአትና ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣<br>የሰፋፊና መካከለኛ የንግድእርሻዎች ዝርዝር ፍሬም (ሪጀስተር)፣ | ሰፋፊ የንግድ እርሻዎችን አስመልክቶ በመረጃ ላይ የተደገፈ ስትራቴጂ ዕቅድና መርሃ-ግብር ለማውጣት ያስቸግራል፣<br>በሰፋፊና መካከለኛ እርሻዎችን አስመልክቶ ምርምር ለመስራት አያስችልም፣ | ከፍተኛ |

የተቋሙ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት... የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ/ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | የተጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የማያስከትለው ተጽዕኖ | የተገልጋዮች/ባለ ድርሻ አካላት ተጽዕኖ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | የተፈጥሮ ሀብትና ከባቢ ስታቲስቲክስ መረጃ | ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>የግብርና ሚ/ር<br>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>የክልል ግብርና ቢሮዎች<br>FAO<br>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን<br>የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>የኢንቨስትሜንት ጽ/ቤት<br>ተመራማሪዎች<br>የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን<br>የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር | መረጃው የሚሰበሰብበትና የማጠናቀርበት የሜቶዶሎጂ እገዛ ማድረግ፣<br>ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር፣<br>ዋና ዋና አመላካቾችን (indicators) በመለየት ሥራ ትብብር ማድረግ፣ | በደን፣በረግረግና በውሃ የተያዘ የመሬት ስፋት በመቶኛ፣<br>የአፈርና ውሃ ጥበቃ መረጃ<br>የአስተራረስ ሁኔታ መረጃ፣<br>የአፈር መሸርሸር ሁኔታ መረጃ<br>የዓሣ ምርት መጠን፣<br>የማገዶ ምርት መጠን፣<br>የአደንና ዱር አራዊት ሁኔታ መረጃ፣ | የተፈጥሮ ሀብትና ከባቢ (Environment) አስመልክቶ ትክክለኛ ፖሊሲ ለማዘጋጀት አስቸጋሪ ነው | ከፍተኛ |
| 9 | በገጠር ያሉት ቤተሰቦች ከግብርና ውጭ የተሠማሩባቸው ሥራዎች (Non-farm) መረጃ | ጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>የግብርና ሚ/ር<br>የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>የክልል ግብርና ቢሮዎች<br>FAO<br>የንግዱ ህብረተሰብ<br>የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>ተመራማሪዎች<br>WB<br>ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ህብረተሰቡ | ጥልቅ ትንተና በሚያስፈልጎቸው መረጃዎች ላይ የቴክኒክ እገዛ በማድረግ በጋራ መሥራት፣<br>የፋይናንስና የሰው ኃይል ሥልጠና እገዛ፣<br>ትክክለኛ መረጃ በመስጠት መተባበር፣ | በገጠር ከግብርና ውጭ ቤተሰቦች የተሠማሩባቸው ሥራዎችዓይነትና የገቢ መጠን፣<br>በገጠር ያሉት ቤተሰቦች የኑሮ ለውጥ አመላካቾች፣<br>በገጠሩ ያለ ህብረተሰብ የጊዜ አጠቃቀም ሁኔታ፣<br>የምግብ ዋስትና ሁኔታ፣ | በገጠር ከግብርና ውጭ እየተካሄደ ያለውን ሥራና ለውጦች ለማወቅ ስለማይቻል ትክክለኛ ፖሊሲ/ ስትራቴጂ መንደፍ አለመቻል፣ | ከፍተኛ |

የተቋሙ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት.. የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች | ተገልጋዮች /ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች /ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከተቋሙ የሚፈልጋቸው ምርት አግልግሎት | የተጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተጽእኖ | ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ተጽእኖ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የዋጋ እና ተያያዥ የድህነት መለኪያ ስታቲስቲክስ<br>• የችርቻሮ ዋጋ መረጃ<br>• የአምራች ዋጋ መረጃ<br>• የቤተሰብ ገቢ ፍጆታና ወጭ መረጃ<br>• የማህራዊ ደህንነት መረጃ<br>• የሥራ ስምሪት ጥናት | • የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት፣<br>• የኢኮኖሚ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩቶች፣<br>• ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር፣<br>• ጤና ጥበቃ ሚ/ር<br>• ንግድ ሚ/ር<br>• ኢንዱስትሪ ሚ/ር<br>• ትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ር<br>• ብሔራዊ ባንክ<br>• ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ<br>• ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት<br>• አለም ባንክ<br>• IMF<br>• ሌሎች የአገር ውስጥ፣ አህጉራዊና አለም አቀፍ ተቋማት | • በዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች/ ኢንዲኬተር ዝርዝር ላይ አስተያየት<br>• ለመረጃው ጥራት ግብአት የሚሆኑ የምርምር ውጤቶች<br>• ለመረጃ አሰባሰብ የፋይናንስ እገዛ<br>• የአቅም ግንባታ እገዛ<br>• ማስኤ በሚያዘጋጀው የአስተያየት መሰብሰቢያ መድረክ ለጥናቶቹ ተገቢውን ግብአት መስጠት | • ጥራቱን የጠበቀ የዋጋ መረጃ በወቅቱ ማግኘት (CPI, PPI…) | ተጠቃሚው በወቅታዊና ትክክለኛ ውሣኔ እንዳይሰጥ ያደርጋል:: | ከፍተኛ |
| | | | | • ለብሔራዊ አካውንት ግብአት የሚሆኑ መረጃዎችን በጥራትና በወቅቱ ማግኘት | በብሔራዊ አካውንት የሚሰሉ ስሌቶች ጥራታቸውና ወቅታዊነታቸው እንዳይጠበቁ ያደርጋል | |
| | | | | • በብሔራዊ አካውንት ዘርፍ ጥራት ያለው መረጃ | በመስኩ ትክክለኛ የፖሊሲ ውሳኔ እንዳይሰጥ ያደርጋል | |
| | | | | • Poverty mapping በመጠቀም መረጃ ማውጣት | በቀላሉ ሊታይ የሚችል(visible) መረጃ ያሳጣል | |
| | | | | • በአነስተኛ አስተዳደር እርከን መረጃ | በአነስተኛ አስተዳደር እርከን ፖሊሲ ለመቅረጽ ተገቢውን መረጃ ያሳጣል | |
| | | | | • Panal survey መጠቀም | በተከታታይ ያለውን ለውጥ በትክክል ለመከታተል ያስቸግራል | |
| | | | | • የquantitative መረጃን በ qualitative information ለመደገፍ ተሳትፎአዊ የድህነት ጥናት ማድረግ (participatory poverty assessment) | Quantitative መረጃውን የበለጠ ተአማኒነት እንዲኖረው በ qualitative information እንዳይደገፍ ያደርጋል:: | |
| | | | | • የውጭው የዋጋ ለውጥ በአገር ወስጥ ኢኮኖሚ ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመከታተል import and export price indices | የውጭው የዋጋ ለውጥ በአገር ወስጥ ኢኮኖሚ ላይ ያለውን ተጽእኖ መከታተል ያስቸግራል:: | |
| | | | | • የቤተሰብ በጀትና ማህበራዊ ደህነነት ጥናት መረጃ ጥራቱን ማሻሻል የሚያስችሉ ዘዴዎችን በመተግበር ውጤቱን በወቅቱ ማቅረብ | በመስኩ ትክክለኛና ወቅታዊ የፖሊሲ ውሣኔ እንዳይሰጥ ያደርጋል:: | |

የተቋሙ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት.. የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች | ተገልጋዮች /ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች /በለድርሻ አንላት የሚፈልጋቸው | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከተቋሙ የሚፈልጋቸው ምርት አግልግሎት | የተጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተጽእኖ | ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ተጽእኖ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ስነህዝብ፣ጤና፣ ትምህርትና የስራ ሁኔታ ስታቲስቲክስ<br>• የህዝብ ብዛት መረጃ<br>• የወሳኝ ኩነቶች መዝገብ<br>• ስነህዝብና ጤና መረጃ<br>• በቆጠራ መሀል (inter censal ) የሚሰበሰብ መረጃ<br>• በጤናና በትምህርት ዘርፍ ከአስተዳደር መዛግብት የሚገኝ መረጃ | • ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>• ህዝብ ተወካዮችና ፌዴሬሽን ምክር ቤት<br>• ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር<br>• ጤና ጥበቃ ሚ/ር<br>• ክልል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ<br>• ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት<br>• UNFPA<br>• ሌሎች የአገር ውስጥ፣ አህጉራዊና አለም አቀፍ ተቋማት | • በዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች/እንዲኬተር ዝርዝር ላይ አስተያየት<br>• ለመረጃው ጥራት ግብአት የሚሆኑ የምርምር ውጤቶች<br>• ለመረጃ አሰባሰብ የፋይናንስ እገዛ<br>• የአቅም ግንባታ እገዛ<br>• ማስኤ በሚያዘጋጀው የአስተያየት መሰብሰቢያ መድረክ ለጥናቶቹ ተገቢውን ግብአት መስጠት<br>• የህዝብና ቤት ቆጠራ ስራ ለማከናወን በየደረጃው የቅንጅት ስራ መፍጠር<br>• በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ስለስታቲስቲክስ የማስተዋወቅ ስራ መስራት | • ወቅታዊ የሆነ የህዝብ ቁጥር መረጃ | ህዝብ ቁጥር ላይ ተመስርተው የሚወስኑ ውሳኔዎችን ያዛባል:: | ከፍተኛ |
| | | | | • በቆጠራ መሃል የሚካሄድ ጥናት (inter censal survey) መረጃ | የቆጠራ መረጃዎችን የሚደግፉና ለፕሮጀክሽን ስራ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ያሳጣል:: | |
| | | | | • የህዝብ ቁጥር ትንበያ (Popn projection) መረጃ በወረዳ ጭምር | በወረዳ ደረጃ የህዝብ ቁጥርን መሰረት ያደረጉ ውሳኔዎችን ያዛባል:: | |
| | | | | • የወሳኝ ኩነቶች መረጃ | የወሳኝ ኩነቶች መረጃ መሰረት የሚያደርጉ ፖሊሲዎች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል:: | |
| | | | | • ወቅታዊ የስነህዝብና ጤና ጥናት ውጤት | በጥናቱ ውጤት ላይ የሚመሰረቱ ፖሊሲዎች ላይ ተጽእኖ ያሳድራል:: | |
| | | | | • የፍልሰት መረጃ | በጥናቱ ውጤት ላይ የሚመሰረቱ ፖሊሲዎች ላይ ተጽጽኖ ያሳድራል:: | |
| | | | | • የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ማከናወንና በናሙና ጥናትና በትምህርት (management information system) ውጤት መሃል ያለውን ልዩነት ማጥበብ | የመረጃ ልዩነት በመፍጠር ተጠቃሚውን ያደናግራል:: | |
| | | | | • አመታዊ ሪፖርት ከትምህርት MIS ማውጣት | በመስኩ ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን ያሳጣል:: | |
| | | | | • የትምህርት መረጃ በ WMS ጥናት መሰብሰብ | የመረጃ ክፍተት ይፈጠራል:: | |
| | | | | • ስለ Morbidity እና የሞት መረጃ መንስኤ በወረዳ ደረጃ መረጃ | የመረጃ ክፍተት በመፍጠር ለፖሊሲ ቀረፃ አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጥራል | |
| | | | | • የጤና ጥበቃ እና ማስኤ መረጃ በጽንሰሃሳብ ምደባ እና የመረጃ ፍላጐት ቅንጅት መፍጠርና የጋራ የመረጃ ቋት መፍጠር | የሚጋጩ መረጃዎችን በመልቀቅ ተጠቃሚውን ማደናገር:: | |
| | | | | • ወቅታዊ የሆነ የማህበራዊ ደህንነት ጥናት | መጃውን በመጠቀም የሚቀረፁ ፖሊሲዎችን ያስተጓጉላል:: | |
| | | | | • ለአደጋ ተገላጭ የሆነውን ህብረተሰብ የሚያሳይ መረጃ | የመረጃ ክፍተት በመፍጠር ተገቢውን ፖሊሲ እንዳይቀረጽ ያግዳል:: | |
| | | | | • የወጣቶችና ዕድሜአቸው ከ10 ዓመት በላይ ለሆናቸው የስራ አጥነት ሁኔታ መረጃ | የመረጃ ክፍተት በመፍጠር ተገቢውን ፖሊሲ እንዳይቀረጽ ያግዳል:: | |
| | | | | • Informal sector የስራ ሁኔታ መረጃ | የመረጃ ክፍተት በመፍጠር ተገቢውን ፖሊሲ እንዳይቀረጽ ያግዳል:: | |
| | | | | • ፕሮፌሽናልና የተማረ ሰው ሃይል አቅርቦት መረጃ | የመረጃ ክፍተት በመፍጠር ተገቢውን ፖሊሲ እንዳይቀረጽ ያግዳል:: | |
| | | | | • Wage index መረጃ | የመረጃ ክፍተት በመፍጠር ተገቢውን ፖሊሲ እንዳይቀረጽ ያግዳል:: | |
| | | | | • ወቅታዊ የስራ ሁኔታ ጥናት ውጤት | የመረጃ ክፍተት በመፍጠር ተገቢውን ፖሊሲ እንዳይቀረጽ ያግዳል:: | |
| | | | | • በዖታ የተከፋፈለ መረጃ እና Time use survey መረጃ | የመረጃ ክፍተት በመፍጠር ተገቢውን ፖሊሲ እንዳይቀረጽ ያግዳል:: | |

# የተቋሙ ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ትንተና

| ተራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች/ባለ ድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ስታቲስቲክስ<br><br>12.1 የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ስታቲስቲክስ<br><br>12.2 የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪዎች ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር<br>- የንግድ ሚኒስቴር<br>- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ብሔራዊ ባንክ<br>- የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- WB<br>- IMF<br>- UNIDO<br>- UNSD<br>- የክልል ቢሮዎች<br><br>- የንግዱ ሕብረተሰብ<br>- ተመራማሪዎች<br>- ሕብረተሰቡ<br>- የማምረቻ ድርጅቶች | • የአሠራር ሜቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል ግብአት በመስጠት<br><br>• የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ፣<br><br>• ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር፣<br><br>• የጥናቶች ፍሬም በመስጠት፣<br><br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የምርት መጠንና ዋጋ<br>- የተሰማራ የሰው ኃይል<br><br>- ተጨማሪ እሴት (Value added)<br><br>- አቅምን የመጠቀም ሁኔታ (capacity utilization)<br>- የመዋዕለ ነዋይ ሁኔታ<br>- የስርጭት ሁኔታ<br>- ዋና ዋና የዕድገት ጠቋሚዎች ...ወዘተ | - ለአጠቃላይ የኢንዱስትሪ ልማትና ዕድገት እና ዕቅድ እንዲሁም ለብሔራዊ አካውንት ወቅታዊና ዓመታዊ ዝርዝር መረጃዎች ለማሟላት ስለማይቻል፣ የዘርፉን ልማት የሚመለከቱ ፖሊሲዎችና ዕቅድ ለማዘጋጀት፣ ለመተንተን፣ ለመከታተል፣ ለመገምገም አለመቻሉ:: | ከፍተኛ |

| ተ ራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች/ባለ ድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | የንግድ ስታቲስቲክስ<br>13.1 የአከፋፋይ ንግድ (Distributive Trade) ስታቲስቲክስ<br>13.2 የገቢና ወጪ ንግድ(Import – export) ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>- የንግድ ሚኒስቴር<br>- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ብሔራዊ ባንክ<br>- የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>- **wB**<br>- **IMF**<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- የክልል ቢሮዎች<br>- የንግዱ ሕብረተሰብ (Investors)<br>- ተመራማሪዎች<br>- የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች<br>- ሕብረተሰቡ<br>- COMESA<br>- UNSD<br>- የጅምላና ችርቻሮ ንግድ ድርጅቶች<br>- አስመጪና ላኪ ድርጅቶች ድንበር አካባቢ ነዋሪ የሆኑ<br>- ነዋሪዎች (ነጋዴች) | • የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል ግብአት የሚሆን፣<br>• የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ መስጠት<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• የጥናቶች ፍሬም በመስጠት፣<br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የስርጭት ሁኔታ<br>- ዋና ዋና የዕድገት ጠቋሚዎች በዘርፉ<br>- የተሰማራ የሰው ኃይል<br>- ተጨማሪ እሴት<br>- ዘርፉ ያሉበት ችግሮች<br>- ወደ አገር የገባ ዕቃ በመጣበት አገር<br>- ወደ ውጪ የወጣ ዕቃ በሄደበት አገር<br>- ከውጪ ንግድ የተገኘ ገቢ<br>- የንግድ ሚዛን<br>- ገቢ ዕቃ በዋለበት ዘርፍ (Import– end use) | የንግድ ዘርፉን የዕድገትአቅጣጫ ወቅታዊና ጠቋሚ ዝርዝር መረጃዎች ለማስገኘት ስለማይቻል የዘርፉን ዕድገትና ፖሊሲ ለመቅረጽ፣ ለመከታተልና ለመገምገም አለመቻል፡፡ | ከፍተኛ |

| ተ ራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላትየሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች/ባለ ድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | የአገልግሎት ንግድ ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>- የንግድ ሚኒስቴር<br>- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ብሔራዊ ባንክ<br>- የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>- IMF<br>- World Bank<br>- UNSD<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- የክልል ቢሮዎች<br>- የንግዱ ሕብረተሰብ (Investors)<br>- ተማሪዎች<br>- ተመራማሪዎች<br>- ሕብረተሰቡ<br>- የአገልግሎት ንግድ ሰጪ ድርጅቶች | • የአሠራር ሜቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች<br>• የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ<br>• ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር<br>• የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል የፋይናንብና የቴክኒክ እገዛ መስጠት<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የስርጭት ሁኔታ<br>- ዋና ዋና የዕድገት ጠቋሚዎች<br>- የተሰማራ የሰው ኃይል<br>- የተፈጠረ ተጨማሪ እሴት<br>- የተገኘ የውጭ ምንዛሪ መጠን<br>- ያሉ ሆቴሎች ብዛት፣ ስርጭት ደረጃ | የአገልግሎት ዘርፉን የዕድገት አቅጣጫ፣ ወቅታዊና ጠቋሚ ዝርዝር መረጃዎች ለማስገኘት ስለማይቻል ለዕቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ መነሻ የሚሆን መረጃ አለማግኘት፡፡ | ከፍተኛ |

| ተራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች /ባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>- የኢንዱስትሪ ሚ/ር<br>- የንግድ ሚኒስቴር<br>- የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ሚ/ር<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ብሔራዊ ባንክ<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- የንግዱ ሕብረተሰብ (Investors)<br>- ተማሪዎች<br>- ተመራማሪዎች<br>- ሕብረተሰቡ<br>- ቤተሰቦች<br>- ት/ቤቶች<br>- ድርጅቶች<br>- የአገልግሎት አቀራቢ ድርጅቶች<br>- ITU<br>- UNECA<br>- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መገናኛ ሚኒስቴር | • የአሠራር ሜቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል ግብአት የሚሆኑ መረጃዎች<br>• የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ<br>• ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር<br>• የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል የፋይናንብና የቴክኒክ እገዛ መስጠት<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የስርጭት ሁኔታ<br>- በህብረተሰቡ<br>- በት/ቤቶች<br>- በሥራ ቦታዎች<br>- ያስገኘው ጥቅም<br>- በህብረተሰቡ<br>- በት/ቤቶች<br>- በሥራ ቦታዎች<br>- በዘርፉ የተሰማራው ኃይል<br>- በዘርፉ የዋለ መዋዕለ ነዋይ (Investment)<br>- የፈጠረው ተጨማሪ እሴት (Value added) | የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂአቅርቦት፣ አጠቃቀምና ያስገኘውን ውጤት የሚያሳዩ መረጃዎች ማስገኘት<br><br>የዘርፉን ዕድገት ለመተለም፣ ለመከታተልና ለመገምገም አለመቻል | ከፍተኛ |

| ተራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራ-ዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላትየሚፈልጋቸውምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | የኮንስትራክሽን ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>- የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ብሔራዊ ባንክ<br>- የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>- World Bank<br>- IMF<br>-UNSD<br>- በዘርፉ መሰማራት የሚፈልጉ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት (Investors)<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- ተመራማሪዎች<br>- ተማሪዎች<br>- ሕብረተሰቡ<br>- ኮንትራክተሮ<br>- ቤተሰቦች<br>- የኮንስትራክሽን<br>- ድርጅቶች | • የአሠራር ሜቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል ግብአት መረጃዎች የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ<br>• ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር<br>• የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል የፋይናንብና የቴክኒክ እገዛ መስጠት<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• ኮንስትራክሽን ኢንዴክስ ለማስላት የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ መስጠት<br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የግንባታ ውጤቶች ዋጋ(Value of construction put in place)<br>- የተሰማራ የሰው ኃይል ብዛት<br>- የተፈጠረ ተጨማሪ እሴት (Value added)<br>- ጥቅም ላይ የዋለ ግብዓት (inputs)<br>- ዋና ዋና የዕድገት ጠቋሚዎች<br>-ዘርፉ ያሉበት ችግሮች | የኮንስትራክሽን ዘርፉን የዕድገት አቅጣጫ ጠቋሚና ወቅታዊ ዝርዝር መረጃዎች ለማስገኘት ስለማይቻል የዘርፉን ዕድገት ለማቀድ፣ ለመከታተልና ለመገምገም አለመቻል:: | ከፍተኛ |

| ተራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | የማዕድንና ቁፋሮ ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ብሔራዊ ባንክ<br>- የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት<br>- የማዕድንና ውሃ ሚኒስቴር<br>- በዘርፉ መሰማራት የሚፈልጉ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት (Investors)<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- ተመራማሪዎች<br>- ተማሪዎች<br>- UNSD<br>- World Bank<br>- IMF<br>- ሕብረተሰቡ<br>- በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች | • ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የተሰማራ የሰው ኃይል ብዛት<br>- የተመረተ ማዕድን መጠን፣ ዓይነትና ዋጋ<br>- የተፈጠረ ተጨማሪ እሴት (Value added) መጠን<br>- ዋና ዋና የዕድገት ጠቋሚዎች<br>- ዘርፉ ያሉበት ችግሮች | የዘርፉን የዕድገት አቅጣጫ ጠቋሚና ወቅታዊ ዝርዝር መረጃዎች ለማስገኘት ስለማይቻል የዘርፉን ልማት ለማቀድ ፖሊሲ ለማውጣት፣ ለመከታተልና ለመገምገም አለመቻል፡፡ | |

| ተራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ ከፍተኛ |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 18 | የኢነርጂና ውሃ ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር<br>- የኢነርጂ ሚ/ር እና የኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ብሔራዊ ባንክ<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- የንግዱ ህብረተሰብ<br>- UNSD<br>- World Bank<br>- IMF<br>- ተመራማሪዎች<br>- ተማሪዎች<br>- የውሃ ሀብት ሚኒስቴር<br>- ሕብረተሰቡ<br>- የማምረቻ ድርጅቶች<br>- የኢነርጂና ውሃ አቅርቦት ሰጪ ድርጅቶች<br>- ድርጅቶች | • የአሠራር ሜቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ<br>• ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የኃይል አቅርቦት መጠንና ስርጭት<br>- የውሃ አቅርቦት መጠንና ስርጭት<br>-ያለው የኃይል አቅርቦት ጥያቄ (Demand<br>- በዘርፉ የተሰማራው የሰው ኃይል<br>- የተፈጠረው ተጨማሪ እሴት (Value added)<br>- የመዋዕለ ነዋይ ፍሰት (Investment) | የዘርፉን የዕድገት አቅጣጫ ጠቋሚና ወቅታዊ ዝርዝር መረጃዎች ለማስገኘት ስለማይቻል የፖሊሲና የዕቅድ ዝግጅት እንዲሁም ክትትልና ግምገማ ለማድረግ አለመቻል:: | |

| ተራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች /ባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | መደበኛ ያልሆነ የሥራዘርፍ (Informal Sector) እና የጎጆ ኢንዱስትሪ ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት<br>- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር<br>- የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር<br>- የንግድ ሚኒስቴር<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- ተመራማሪዎች<br>- UNSD<br>- World Bank<br>- IMF<br>- መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት<br>- የከተማ መስተዳድሮች<br>- የሥራው አንቀሳቃሾች (Operators)<br>- የማምረቻ ድርጅቶች | • የአሠራር ሜቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ<br>• ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር<br>• የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ መስጠት<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ድርጅቶች የምዝገባ ሥርዓትን ማሻሻልና ለስታቲስቲክስ ጥቅም እንዲውል ማድረግ<br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የተሰማራው የሰው ኃይል በፆታ<br>- የተፈጠረው ተጨማሪ እሴት (Value added)<br>- ያሉበት ችግሮች<br>- የሚያስፈልገው ዕገዛ ዓይነት | የዘርፉን ሁኔታ ጠቋሚ ወቅታዊ መረጃዎች ለማስገኘት ስለማይቻል የፖሊሲና የዕቅድ ዝግጅት ትንተና፣ ክትትልና ግምገማ ለማድረግ አለመቻሉ፡፡ | ከፍተኛ |

| ተራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራዎች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት የሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች /ባለድርሻ አካላት ተፅዕኖ ደረጃ ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 20 | የትራንስፖርትና መገናኛ ስታቲስቲክስ | - የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት<br>- የትራንስፖርት ሚኒስቴር<br>- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር<br>- ብሔራዊ አካውንት<br>- ፖሊሲ አውጪዎች<br>- ተመራማሪዎች<br>- መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት<br>- የከተማ መስተዳድሮች (Investors)<br>- የትራንስፖርት ድርጅቶች /ማኅበራት<br>- የሬዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት<br>- ትምህርት በመገናኛ ዘዴዎች ድርጅት<br>- IMF<br>- World Bank<br>- UNSD<br>- ጋዜጣና መጽሔት አሣታሚዎች<br>- የምድር ባቡር ኩባንያ<br>- የኢትዮጵያ ንግድ መርከብ<br>- የኢትዮጵያ አየር መንገድ | • የአሠራር ሜቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ<br>• ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>• ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር | - የተጓጓዘ መንገደኛ ብዛት<br>- የተጓጓዘ ዕቃ መጠን ደረቅና ፈሳሽ<br>- የተሽከርካሪ ብዛትና ዓይነት<br>- የትራንስፖርት ታሪፍ<br>- የመንገዶች ርዝመትና ዓይነት<br>- የዋለ መዋዕለ ነዋይ<br>- የሕትመት ውጤቶች ብዛትና ስርጭት<br>- የቴሌቪዥንና ሬዲዮ -አገልግሎት ስርጭት በዓይነት<br>- ትምህርት በመገናኛ ብዙኃን ስርጭት | የዘርፉን የዕድገት አቅጣጫ ጠቋሚና ወቅታዊ ዝርዝር መረጃዎች ለማስገኘት ስማይቻል ለፖለሲ፣ ለዕቅድ፣ ለግምገማና ክትትል ለማድረግ አይቻልም:: | |

| ተራ ቁ. | የሚከናወኑ ዝርዝር ሥራች | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላትየሚፈልጋቸው ምርት/አገልግሎት | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላትየሚፈልጓቸው ምርት/አገልግሎት | የሚጠበቀው ውጤት ባይሟላየሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተፅዕኖ | የተገልጋዮች/ ባለድርሻ አካላትተፅዕኖ ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | የስታቲስቲክስ ቢዝነስ ሬጂስተር መረጃ አቅርቦት | - ናሽናል አካውንት<br>- ኢኮኖሚያዊ ጥናት<br>የሚያካሂዱ<br>- የመንግሥት ተቋማት<br>- የግል ተቋማት<br>- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች<br>- ተመራማሪዎች<br>- ተማሪዎች<br>- ክልል ቢሮች<br>- የቢዝነስ ተቋማት<br>- በተለያዩ መ/ቤቶች ያሉ የቢዝነስ ሬጂስተሮች/ዳይሬክተሮች | • የአሠራር ሜቶዶሎጂዎችን ለማሻሻል የፋይናንስና የቴክኒክ እገዛ ማድረግ<br>• ከአስተዳደራዊ መዛግብት የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት መተባበር<br>• የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል የፋይናንብና የቴክኒክ እገዛ መስጠት<br>• ማሻሻያ በሚያስፈልጋቸው አማላካቾች (indicators) ላይ የማሻሻያ አስተያየት መስጠት<br>- ወቅቱን የጠበቀና ጥራት ያለው መረጃ በመስጠት መተባበር<br>- ሬጂስትሮቻቸውን ለስታቲስቲክስ አገልግሎት እንዲሆን አድርጎ ማደራጀት፣ ወቅታዊ ማድረግ | - የቢዝነስ ሬጂስተር ሲስተም መፍጠር<br>- ለሚካሄዱ ኢኮኖሚ ነክ ጥናቶች baseline data ማስገኘት<br>- የቢዝነስ ተቋማትን ብዛትና ስርጭት በኢንዱስትሪ ዘርፍ ማስገኘት<br>- ለብሔራዊ አካውንት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎች ማስገኘት<br>- ለኢንቨስተመንት ግብዓትየሚሆን መረጃ | - የተሟላና ወቅታዊ (up-to-date) የሆነ የሬጂስተር ሲስተም ለማስገኘት አለመቻል::<br>- የናሙና ጥናቶችን ማጥናት አለመቻል:: | በጣም ከፍተኛ |

የተቋሙ ተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት.. የቀጠለ

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች | ተገልጋዮች /ባለድርሻ አካላት | ተቋሙ ከተገልጋዮች /በለድርሻ አካላት የሚፈልጋቸው | ተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት ከተቋሙ የሚፈልጋቸው ምርት አግልግሎት | የተጠበቀው ውጤት ባይሟላ የሚኖረው ምላሽና የሚያስከትለው ተጽእኖ | ከተገልጋዮች ባለድርሻ አካላት ተጽእኖ ድርሻ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 22 | የመረጃ ጥራት<br>• ጽንሰሃሳብና ፍቺ፣ምደባ፣<br>• ስያሜና ኮዲንግ ዝግጅት<br>• የአቅም ግንባታ ስራ<br>• የመረጃ ጥራት ቁጥጥር መስፈርት ዝግጅትና ትግበራ<br>• የስታቲስቲክስ ሲስተም ቅንጅት | • ሴክተር መ/ቤቶች<br>• የምርምር ተቋማት<br>• ፖሊሲ አውጭዎች<br>• የሙያ ማህበራት<br>• አህጉራዊና አለም አቀፍ ተቋማት | • በጋራ ስምምነት የተደረሰባቸውን ጽንሰሃሳቦችና ምደባዎች ተግባር ላይ ማዋል<br>• የተቀናጀ ስራ<br>• የመግባቢያ ስምምነት መፈረምና መተግበር<br>• የመረጃ ጥራትን ለመከታተል የሚያስችለ የተለያዩ የምርምር ውጤቶች<br>• የመረጃ ጥራት ቁጥጥርን ለመስራት የሚያስችል የቴክኒክና የገንዘብ ዕገዛ | • ወጥ የሆነ ጽንሰሃሳብና ፍቺ ማዘጋጀትና በአጠቃላይ በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ መተግበር | • የተለያዩ ጽንነሰሃሳቦች በመጠቀም በስታቲስቲክስ ሲስተሙ የመረጃ ግጭት ይፈጥራል:: | ከፍተኛ |
| | | | | • የተቀናጀ የስታቲስቲክስ ሲስተም በሃገሪቱ መፍጠር | • በቅንጅት ጉድለት የመረጃ ድግግሞሽ በመፍጠር የሃብት ብክነት | |
| | | | | • ወጥ የሆነ አሰራር በመዘርጋት በተለያዩ አካላት የሚወጡ መረጃዎች ልዩነትን ማጥበብ | • በተለያዩ አካላት የሚወጡ የሚጋጩ መረጃዎች | |
| | | | | • የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን አቅም መገንባት | • በአቅም ውሱንነት ተገቢውን የመረጃ ጥራት ቁጥጥር አለማከናወን | |
| | | | | • ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር የቅርብ ውይይት ማድረግ | • የተጠቃሚዎችን ፍላጐት ያላገናዘበ መረጃ | |
| | | | | • መረጃዎች ወቅታቸውን ጠብቀው እንዲወጡ ማድረግ | • መረጃውን ተመስርተወ የሚወሰኑ ውሳኔዎችን ያዘገያል | |
| | | | | • የመረጃ ጥራት ቁጥጥር መስፈርት በማዘጋጀት በስታትስቲክስ ሲስተም የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ማከናወን | • የመረጃውን ተአማኒነት ይቀንሳል:: | |
| | | | | • ጥራታቸው የተረጋገጡ መረጃዎችን በአንድ የመረጃ ቋት ማስቀመጥ | • መረጃ በቀላሉ እንዳይገኝ በማድረግ የመረጃ እጥረት ይፈጥራል | |

# ክፍል 6

## 6. የኤጀንሲው ተልዕኮ ከአገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር ያለው ትስስር ትንተና፣

መንግስት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሰፈነባት ኢትዮጵያ ለመገንባትና የአገሪቱን ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ለማፋጠን፣ በአጠቃላይ ድህነት በመቅረፍ የበለፀገች ኢትዮጵያ ለመገንባት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች በመቅረፅና በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ መሠረት እያንዳንዱ የመንግስት አስፈፃሚ አካል (የመንግስት መ/ቤቶች) በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የመንግስት ፖሊሲዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት በመከተል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

<u>መንግስት የዘረጋቸው ዋና ዋና ፖሊሲዎች:-</u>

1. የዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ
2. የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ
3. የውጭ ጉዳይና አገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ
4. የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ
5. የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራሞች ናቸው፡፡

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ተልዕኮ ለልማት ፖሊሲዎች ቀረፃ፣ ለዕቅድ ዝግጅት ለክትትልና ግምገማ ግብዓት የሚሆኑ ወቅታዊና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ስታቲስቲካል መረጃ ማቅረብ ሲሆን ከላይ ከተጠቀሱት አገራዊ ፖሊሲዎች መካከል ከአብዛኞቹ ጋር የሚኖረውን ትስስር በአጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 6.1 የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጉዳዮች

በዚህ ፖሊሲ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑም ከኤጀንሲው ተልዕኮ ጋር ትስስር የሚኖራቸው የሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎና ያልተማከለ አስተዳደር ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማጎልበት ለሚደረገው እንቅስቃሴ ኤጀንሲው በየ10 ዓመቱ በሚያካሄደው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሚሰበሰበው የሕዝብ ብዛት የሚያሳይ መረጃ በወረዳና በቀበሌ በማቅረብ በእያንዳንዱ ክልልና ወረዳ ሊኖር የሚገባው የምርጫ ክልልና የሕዝብ ተወካዩች ብዛት ለመወሰን ዋና ግብዓት በመሆን ያገለግላል፡፡ ሌሎችም በኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፍ የሚደረጉ የስታቲስቲክስ ጥናቶች የዕድገትና የድህነት ፖሊሲ አመላካች ጠቋሚ አሃዝ ስለሚያስገኙ የዕኩልነት እና የዕኩል ተጠቃሚነት ዲሞክራሲያዊ መርህን ለመተግበር ግብአት የሆኑ መረጃዎችን ያስገኛል፡፡

## 6.2 የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ

የገጠር ልማት ፖሊሲ ከሚያተኩርባቸው አቅጣጫዎች አንዱ የእርሻ መሬትን በአግባቡ በመጠቀም የግብርና የምርትና ምርታማነትን ማሣደግ ነው። ኤጀንሲው በየዓመቱ የግብርና ናሙና ጥናት (Sample Survey) በማካሄድ የታረሰ መሬት ስፋት፣ ከእያንዳንዱ የሰብል ዓይነት የተገኘ የምርት መጠን በሄክታር፣ እንዲሁም የቤት እንስሳት ብዛትና ተዋጽኦ (ወተት፣ ሥጋ፣እንቁላል ወ.ዘ.ተ) መጠንና አጠቃቀም፣ የሚያመለክት ስታቲስቲካል መረጃ በመሰብሰብ ለመንግስትና ለተጠቃሚዎች በማቅረብ የግብርናው ዘርፍ በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለመገምገምና ለመከታተል የሚያስችል መረጃ ያቀርባል።

የአርሶ አደሩ ዘመናዊ የግብርና ቴክኖሎጂ (የተሻሻሉ ዘሮችና የግብርና መሣሪያዎች) አጠቃቀም የአርሶ አደሩን አቅም እንዲመጥኑ አድርጎ በማቅረብ በሚፈለገው ብዛትና ጥራት ያለው ፈጣን ሥርጭት ማስፋን በግብርና ፖሊሲው ላይ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ ነው። በመሆኑም ኤጀንሲው በየዓመቱ የግብርና ጥናት በማካሄድ የተሻሻሉ ዘሮች (ምርጥ ዘር) አጠቃቀም አስመልክቶ በየዓመቱ የሚኖረውን ለውጥ ለማነፃፀርና ለመገምገም የሚያስችል የስታቲስቲክስ መረጃ ያቀርባል። የግብርና ቴክኖሎጂ በመጠቀም አርሶ አደሮች በገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በማምረት በተፈለገው ጥራትና ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ ሸጠው ለመጠቀምና በዚህም ሂደት ገበያቸው በቀጣይነት እንድያድግ ይጠበቃል።

ኤጀንሲው አርሶ አደሮች ለገበያ የሚያቀርባቸውን የምርት ዓይነቶች በመለየት የአምራቾች የዋጋ ጥናት ያከናውናል በዚህ ጥናት መጠኑ የሚታወቅ የግብርና ምርት በምን ያህል ዋጋ እደሚሸጡና አርሶ አደሮች በአገር ውስጥ በሚደረገው የነፃ ገበያ ያላቸውን እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ያቀርባል። ከግብርና ውጭ ያሉ የኢኮኖሚና ማህበራዊ የዕድገት ሁኔታዎችን የሚቃኙ "Socio-economic Surveys" በማካሄድ የገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ ተፈጻሚነት የሚቃኙ ጥናቶችን ያከናውናል።

## 6.3 የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ

ኢንዱስትሪው ተገቢውን ትኩረት አግኝቶ ግብርና መር የልማት ስትራቴጅ ባስቀመጠው አቅጣጫና ከግብርና ጋር ተመጋገቢ በሆነ መልኩ በተቻለ ፍጥነት እንዲያድግ ማድረግ የሚጠበቀውን አገራዊ ልማት ለማሳካት ወሳኝ መሆኑንና ከዚሁ ጐን ለጐን አስተማማኝ የመሰረተ ልማት አገልግሎት አቅርቦት መፍጠር ዘማናዊ ለልማት የተመቻቸ የፋይናንስ ሥርዓት (ባንኮችና ሌሎች የፋይናንስ ተቋማት) መፍጠር ኢንዱስትሪን ለማልማትና ድህነትን ቀርፈን አገራችን የሠነቀችውን ራዕይ ላይ ለመድረስ መሠረታዊ ጉዳዮች ናቸው።

የገበያ ኢኮኖሚ በነገሠበት ዘመን በተለይም መላው አለም በኢኮኖሚ በጥብቅ በተሣሠረበት ሁኔታ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ወቅታዊ፣ ትክክለኛና የተሟላ መረጃ መኖር የገበያ ውድድሩ

ውጤታማና ቀልጣፋ ያደርገዋል:: በአሁኑ ወቅት የመረጃና የኮምኒዩኬሽን ቴክኖሎጂ አለምን እየቀየሩ ካሉ ቴክኖሎጂዎች አንዱ እየሆነ መጥቷል::

በመሆኑም የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በአገራችን የሚገኙ አነስተኛና ጥቃቅን ኢንዱስትሪዎችን፣ መካከለኛና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎችን፣ የትራንስፖርት፣ የኢነርጂ ምንጮችን፣ የኤክስፖርት ኢንዱስትሪና ባንኮችን ተያያዥ የዋጋ መረጃዎችንና ኢንዴክሶችን የሚመለከት ስታቲስቲካል መረጃዎች በየወቅቱና በየዓመቱ በመሰብሰብና በማጠናቀር የኢንዱስትሪው ሴክተር የደረሰበትን ደረጃና በየዓመቱ የሚታየውን ዕድገት ለመከታተልና ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለመንግስት፣ ለተመራማሪዎች፣ ለኢንቨስተሮችና ለተጠቃሚዎች ያቀርባል::

## 6.4 የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስትራቴጂና ፕሮግራም

የዚህ ፖሊሲ ትኩረት ብቃት ያለው የሰው ሃይል በቀጣይነት ማፍራት፣ አሰራርና አደረጃጀቶችን በየጊዜው እየገመገሙ አዳዲስ ሃሳቦች በማፍለቅ በቀጣይነት ማሻሻል በሚል መርህ ላይ የተመሠረተ ነው::

የሰው ሃይል ብቃት ለማሳደግ ከአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ጀምሮ እስከ ዩንቨርሲቲ ድረስ የሚዘልቅ የትምህርትና ስልጠና ተቋሞች መኖር የግድ ይላል:: አንድ ተጨባጭ ሙያና እውቀት ያለው፣ ጥሩ የሥራ ስነ-ምግባርና ታታሪነት ተላበሰ የሰው ሃይል በሚፈለገው መጠን ለማፍራት የሚቻለው ይህንን ለመፈፀም የሚችሉ ብቃትና ብዛት ያላቸው የትምህርትና ስልጠና ተቋሞች፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ አቅሞች ሲፈጠሩና በቀጣይነት እየተጠናከሩና እየተስፋፉ ሲሄዱ ነው::

በአገራችን ያሉ የትምህርት ተቋማት በቂ መሆናቸውን ለማወቅ ብዛታቸውና ሥርጭታቸውን በየአካባቢው ካለው ሕዝብ ጋር ማነፃፀር የሚያስችል ስታቲስቲካል መረጃ ያስፈልጋል::

በመሆኑም ኤጀንሲው በሚያከናውነው የሕዝብ ቆጠራ እንዲሁም በየጊዜው በሚያካሂዳቸው ጥናቶች (Survey) በየክልሉ ያለውን የሰው ኃይል በትምህርት ደረጃና በሙያ ዓይነት ብዛቱ ምን ያህል እንደሆነ የሚያመለክት መረጃና በየአካባቢው ያሉ የትምህርት ተቋማት ብዛት የሚያሣይ መረጃ ለመንግስትና ለተጠቃሚዎች ያቀርባል:: በተጨማሪም የሰው ሃይል ግንባታና የትምህርት ተቋማት ብዛት ላይ በየዓመቱ የሚታየውን ለውጥ ለመገንዘብ የሚያስችል አሃዛዊ መረጃ በመሰብሰብና በማጠናቀር አጠቃላይ የሰው ሃይል ዕድገትን ለመገምገምና ለመከታተል የሚያስችል የሥራ ስምሪት ጥናት በየዓመቱ ያካሂዳል::

### 6.5 የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ

የዚህ ፖሊሲ ዓላማ ልማትንና ዲሞክራሲን በአገራችን እውን ለማድረግ የሚያስችል የተመቻቸ የውጭና የደህንነት ሁኔታ መፍጠር ነው። በግሎባላይዜሽን ማዕቀፍ ሥር ሆኖ ልማትን እውን ለማድረግ ሰፊ የገበያ ዕድል፣ ኢንቨስትመንት፣ የብድርና ዕርዳታ እና የቴክኒክ ድጋፍ ያስፈልጋል። እነዚህ ጉዳዮች መጠናቸውና ደረጃቸውን በትክክል ማወቅ የሚቻለው በዝርዝር የተሟላ ጥናት በማድረግ ነው። በአጭር አገላለጽ ጥናት ለማድረግ በአገር ውስጥ ያለውን የሶሽዮ ኢኮኖሚክ ሁኔታ የሚያመለክቱ መረጃዎችን በምንጭነት መጠቀም ያስፈልጋል። ይህም ማለት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የሚያቀርበውን የሶሽዮ ኢኮኖሚክ መረጃ የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንት ግቦችን ለማሳካት በሚደረገው ጥናታዊ እንቅስቃሴ እንደግብዓት ያገለግላል። ይህ አገራዊ ፖሊሲ በዋነኝነት ትኩረቱ የኢኮኖሚ ዕድገት /የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ/ እንደመሆኑ መጠን በኤጀንሲው የሚካሄዱ ጥናቶች የውጪ ኢንቨስትመንት ሁኔታንና የውጪ ንግድ ዕድገት አመልካች መረጃን በማቅረብ የዚህ አገራዊ ፖሊሲን ተፈጻሚነት የሚያመለክቱ መረጃዎችን ያስገኛል።

# ክፍል 7 የተቋሙ ስትራቴጂአዊ የትኩረት መስኮችና ዉጤቶች

## 7.1 የትኩረት አቅጣጫ 1 የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተምን ማስተባበር

ይህ የትኩረት አቅጣጫ መስሪያ ቤቱ በአዋጅ የተሠጠዉን ወጥ ደረጃዎችን፣ ምደባዎችን እና ትርጉሞችን በማዘጋጀት እንዲሁም የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ስልቶችን በማዘጋጀትና በመተግበር የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተምን የማስተባበር ስራን ያመለክታል። የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ስልት ከሜቶዶሎጂ (የአሠራር ስልት) ባለፈ ሁሉን አቀፍ ስልቶችን የሚያቅፍና ዘረፈ ብዙ የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ማዕቀፍ (DQAF) ግብዐቶችን ያካተተ ነው። የጥራት ቁጥጥሩ ሥራ ማስኬ ውስጥ የተቋቋመው የሥራ ሂደት ድርሻ ይሆናል። አስቀድሞ በተወሠነ የጊዜ ሠሌዳ እያንዳንዱ የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብ ጥራት መፈተሽ ይኖርበታል። የቁጥጥሩ ውጤት የሚገለጽና የማሻሻያ መርሀ ግብሩም በስምምነት ላይ የሚመሠረት ይሆናል። የጥራት ማሻሻል ሥራን ለማገዝ እና የስታቲስቲክስ ደረጃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቶችና ኤጀንሲዎች ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ የስታቲስቲክስ ክፍሎች መቋቋም ይኖርባቸዋል።

**የዚህ የትኩረት አቅጣጫ ንዑስ ክፍሎች ፡-**

1.1 ወጥ የሆኑ ስታንዳርዶች፣ ምደባዎች እና ትርጉሞች ለብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ ማዘጋጀትና ለብሔራዊ የስታቲስቲክስ ምክር ቤት (ካውንስል) አቅርቦ ለአገራዊ ስታቲስቲክስ ህግ (መመሪያ) እንዲሆኑ ማፀደቅ፣

1.2 በማስኤ እና የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙ ከልማት አጋሮች መካከል የአገልግሎት አሰጣጥ ስምምነቶችን ተግባራዊ ማድረግ፣

1.3 በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ የስታቲስቲክስ እቅዶችና የልማት አጋሮች መካከል ያለውን እንቅስቃሴ ማስተባበር፣

1.4 የኢትዮጵያን የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ስልት ማዕቀፍ (DQAF-E) ማዘጋጀትና መተግበር፣

1.5 የብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ አባል በሆኑ የሚኒስቴር መ/ቤቶች፣ ኤጀንሲዎች ውስጥ የስታቲስቲክስ ክፍሎችን እንዲቋቋሙ ማገዝ፣

1.6 በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ ውስጥ የአቅም ግንባታ ሥራዎችንና የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ሥራን ለመሥራት እንዲችል ማስኤ ውስጥ ያለውን ይህን ሥራ በኃላፊነት የሚሠራውን ክፍል ማጠናከር፣

1.7 የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ስርዓቱን መምራት፣

## 7.2 የትኩረት አቅጣጫ 2 ስታቲስቲክስን የማስተዋወቅና ጥቅሙን የማስገንዘብ ሥራ በሰፊው መሥራት

የስትራቴጂ ዕቅድ ዶኩመንቱ (NSDS) ሲዘጋጅ ለመገንዘብ እንደተቻለው በባለድርሻ አካላት በኩል ስላለው የስታቲስቲክስ መረጃ ያለው እውቀት ችግሮች እንዳሉት ነው፡፡ በመሆኑም ስለ ስታቲስቲክስ ሥራዎች የማስተዋወቅ ሥራ በሰፊው መስራት ያስፈልጋል፡፡ በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ውጤቶችን የስርጭት መርሀ ግብር (Release Calander) በጋዜጣዊ መግለጫ አስደግፎ ለተጠቃሚዎች ገለፃ ማድረግና ግንዛቤያቸውን ማሣደግ ያስፈልጋል፡፡ ከአንድ የመረጃ ድረ- ገፅ (Web-site) በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ የሚዘጋጁ የስታቲስቲክስ የሥራ ውጤቶች የሚገኙበትን መንገድ ማመቻቸት እና ለተጠቃሚዎች ተጨማሪ ስልጠና መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ስልጠናው በተግባር የተደገፈና ስለጥናቶቹ ዳታቤዝና ሶፍትዌር አጠቃቀምን ማካተት ይኖርበታል፡፡

የዚህ ትኩረት አቅጣጫ ንዑስ ክፍሎች፡-

2.1 ለብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ የጋራ ጥቅም የሚውል ድረ ገፅ ማዘጋጀት

2.2 የጋዜጣዊ መግለጫ አሰጣጥና የስታቲስቲክስ ጥናቶች መጀመራቸውን ማብሰሪያ መንገድ ማሻሻል፣

2.3 ስለ መረጃ አጠቃቀም ለተጠቃሚዎችና ለመገናኛ ብዙሀን ባለሞያዎች ስልጠና መስጠት፣

2.4 ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር ቀጣይነት ባለው መልኩ (በቋሚነት) ውይይቶችን ማድረግ፣

## 7.3 የትኩረት አቅጣጫ 3 የስታስቲክስ መረጃ አቅርቦትና የአሠራር ሥልቶችን (ሜቶዶሎጂን) ዘመናዊ ማድረግ

ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገው ውይይት ለመረዳት እንደተቻለው ያሉት የመረጃ ክፍተቶች ከመለየታቸውም ባሻገር በጥናቶቹ ላይ የሥራ ድግግሞሽ መኖሩና የጥናቶችን አስፈላጊነት ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ ግንዛቤ ተወስዷል። ክፍተቶች እንዳሉና ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ስምምነት ላይ የተደረሰባቸው ዘርፎች የንግድ እርሻ፣ ከባቢ (Environment) ስለአርብቶ አደር ሕዝቦች እና የዋጋና ኢኮኖሚ ዘርፍ ስታቲስቲክስ ጥናቶች በተለይም ኮንስትራክሽን፣ የገቢና ወጪ ንግድ ስታቲስቲክስ ኢንዴክሶች ናቸው። የቢዝነስ ሬጂስትርን ማዋቀርና ማቀናጀት የሞዴሊንግ ቴክኒክ አስቸጋሪ ባህርይ ላላቸው ጥናቶች ሥራ ላይ ማዋል እንደ መጀመሪያ እርምጃ ሊወሰዱ ይችላሉ። በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ አጋሮች በዝቅተኛ አስተዳደር እርከን ላሉ የአገሪቱ ክፍሎች የሕዝብ ብዛት ትንበያ እና የወሳኝ ኩነቶች መረጃ መኖር አስፈላጊነቱ ተጠቁሟል።

የግብርናና የሕዝብ ቆጠራዎች በየአሥር ዓመቱ መካሄድ እንዳለባቸው፣ የናሙና ጥናቶችም በየአምስት ዓመቱ የስታትስቲክስ መርሀ ግብር መሠረት መካሄድ እንዳለባቸው፣ ነገር ግን የቤተሰብ ገቢ፣ ወጪና ፍጆታ ጥናት፣ የማሕበራዊ ደህንነት ጥናት፣ ስለ ኢንፎርማል ሴክተር እና የጎጆ ኢንዱስትሪዎች መረጃ እንዲያስገኙ ማድረግ ያስፈልጋል።

የዚህ ትኩረት አቅጣጫ ንዑስ ክፍሎች፡-

3.1 የተቀናጀ የቤተሰብ ጥናትን አስፈላጊነት ማረጋገጥና ከሌሎች መደበኛ ሲስተሞች ጋር እንዲናበብ ማድረግ፣

3.2 የግብርናና ከባቢ ጥናት ስታቲስቲክስ የአሠራር ስልት (Methodology) ማሻሻል ሽፋኑን ማስፋፋትና የንግድ እርሻን፣ የአርብቶ አደሩን አካበባቢዎች፣ የከባቢ ሁኔታዎችን እና የተፈጥሮ ሀብትን እንዲሸፍን ማድረግ፣

3.3 የግብርና ቆጠራን በማስቀጠል ለግብርና ናሙና ጥናት መነሻ ፍሬምና አስተማማኝ ለሆነ የግብርና ውጤት ማስገኘት፣

3.4 የማሕበራዊ ደህንነት መረጃ በተመለከተ የአሠራር (አጠናን) ስልቱን ማሻሻል Modular ስልት መጠቀም፣ ሽፋኑን ማሳደግ፣

3.5 የቢዝነስ ሬጅስተር ሲስተሙን መዘርጋት፣ ማሻሻልና የመረጃ ምንጮቹን ማቀናጀት፣

3.6 የገቢና ወጪ ንግድ ኢንዴክሶችን ማዘጋጀት፣

3.7 የሥነ ሕዝብ ትንበያ ስራዎችን ማሻሻል፣ የወሳኝ ኩነቶችን ምዝገባ ሥርዐት ማሻሻል እና የተሻሻለ የቱሪዝም ስታቲስቲክስ መረጃ ማስገኘት፣

## 7.4 የትኩረት አቅጣጫ 4 የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን አቅም መገንባት

እየጨመረ የመጣውን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት ለማርካትና በልማት ፖ.ሲ.ሲ. ቀረፃና ክትትል የስታቲስቲክስን ድርሻ ለማጉላት በዘርፉ ኢንቨስት ማድረግ(ሀብት ማፍሰስ) ያስፈልጋል። እስካሁን በተካሄዱ ጥናቶች ላይ የተካሄዱ ጥልቅ ትንተናዎች ውስን ናቸው። ይህም የሆነው የጥልቅ ትንተና ክህሎት አቅም ውሱንነት እና ስለመረጃ ቋቶቹ ያለው እውቀት አናሳ መሆንና እና ለትንተና የሚያግዙ ሶፍትዌሮች አለመኖር ነው። ለዚህም የጥልቅ ትንተና (የምርምር) ክህሎቶችን መገንባት ያስፈልጋል።:

ይህንን በተለይም ከፍተኛ (እውቀትና ክህሎት) ያላቸውን የስታቲስቲክስ እና የICT ባለሙያዎች ለመንግስት ሥራ ማቆየት አስቸጋሪ እየሆነ መጥቷል። እነዚህ ባለሞያዎች ደግሞ የስታቲስቲክስን ሥራ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና ኤጀንሲዎች ያሉ የስታቲስቲክስ ክፍሎችን ለማሸሻል በጣም አስፈላጊ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ተከታታይ የሆነ የክህሎት ማሻሻያ ሥራ መሥራት አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ሠራተኞች በመንግስት ሥራ ላይ ለመቆየት ያላቸውን ፍላጎት ስልጠና እንዲጨምር ያደርጋል። ለዚህም የአጠቃላይ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን የስልጠና ፍላጎት መዳሰስ እና የሥራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

በተለያዩ ምክንያት ከፍተኛ ክህሎትና እውቀት ያላቸው ሠራተኞች ሲለቁ የእውቀት ሽግግር (ማስተላለፍ) ወሳኝ ጉዳይ ነው። በመሆኑም የስታቲስቲክስን እሴት ፍሰትንና ወቅቱን የጠበቀ ሜታ ዳታ (ማብራሪያ) በማዘጋጀት ያለውን ዕውቀት ዶክመንት ማድረግ

ያስፈልጋል። ይህም ሠራተኞች ሥራ በሚለቁበት ወቅት የሥራ ሂደቱ ፍሰት እንዳይቋረጥ ያደርጋል።

ቴክኖሎጂ የመረጃ ጥራትን ወቅታዊነቱን እና ተደራሽነቱን ለማሻሻል በከፍተኛ ሁኔታ ያግዘዋል። ስለሆነም በኮምፒውተር የታገዘ የመረጃ መሰብሰብ እና የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን የግንኙነት ስርዐት ማሻሻል ያስፈልጋል። የሳተላይት ምስልም (Imagery) የስታቲስቲክስ ስራዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመሥራት ይረዳል።

ማስኤ አሁን ያለበት ህንፃ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ሥራ ላይ ለማዋልና በአግባቡ ሥራን ለመምራት አያመችም። ለተሻለ የቡድን ሥራ፣ የሥራ ላይ ሥልጠና እና የብሔራዊ ስታትስቲክስ ሲስተሙን የሥራ ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ አዲስ ሕንፃና የተሻሉ መሣሪያዎች (ግብዐቶች) ያስፈልጋሉ።

### የዚህ ትኩረት አቅጣጫ ንዑስ ክፍሎች

4.1 በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ ውስጥ ያለውን የትንተና ክህሎት ማግደግ፣

4.2 የስታቲስቲሽያኖችን ፣ የICT እና ተዛማጅ ባለሙያዎችን አቅርቦት መጨመር፣

4.3 የሥራ ላይ ሥልጠና እና የእውቀት ሽግግር ዘዴን በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ ውስጥ መዘርጋት፣

4.4 የስታቲስቲክስ ማሕበራትንና የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙ አባላትን የሙያ ክህሎት ማጠናከር፣

4.5 የቴክኖሎጂ አቅርቦትን ማሻሻል (ማጠናከር)፣

4.6 የሕንፃ እና ሌሎች የሥራ ቦታ ሁኔታዎችን ማሻሻል፣

## 7.5. የኤጀንሲው ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች፣ መግለጫዎችና ውጤቶች

| ተ.ቁ | ስትራቴጂአዊ የትኩረት መስኮች | የትኩረት መስኩ መግለጫ | የትኩረት መስኩ ዉጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | የብሄራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን ማስተባበር | ወጥ ደረጃዎችን፣ ምደባዎችን እና ትርጉሞችን በማዘጋጀት እንዲሁም የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ስልቶችን በማዘጋጀትና በመተግበር የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተምን የማስተባበር ስራን ያመለክታል | የተቀናጀ ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተም |
| 2. | ስታቲስቲክስን የማስተዋወቅና ጥቅሙን የማስገንዘብ ሥራ በሰፊው መሥራት | ስለ ስታቲስቲክስ ሥራዎች የማስተዋወቅ ሥራ በሰፊው መስራት፣በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተሙ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ውጤቶችን የስርጭት መርሀ ግብር (Release Calander) በጋዜጣዊ መግለጫ አስደግፎ ለተጠቃሚዎች ገለፃ ማድረግና መረጃ ከአንድ የመረጃ ድረ- ገፅ (Web-site) የሚገኙበትን መንገድ ማመቻቸት | በህብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠረ የተሻለ የስታቲስቲክስ ግንዛቤ |
| 3 | የስታቲስቲክስ መረጃ አቅርቦትና የአሠራር ሥልቶችን (ሜቶዶሎጂን) ዘመናዊ ማድረግ | የመረጃ ክፍተቶች ያለባቸዉን ዘርፎች በመለየትና ተገቢዉን የአሰራር ስልት በመቀየስ በየዘርፉ ተፈላጊዉን መረጃ በጥራትና በወቅቱ ማቅረብ | በየዘርፉ ወቅታዊና ጥራት ያለዉ መረጃ |
| 4 | የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተሙን አቅም መገንባት | የብሄራዊ ስታተቲስቲክስ ሲስተሙ አስተማማኝ አቅም ያለው አባላትን የሙያ ክህሎት ለማሳደግ የስራ ላይ ስልጠናና የእዉቀት ሽግግር ዘዴን መዘርጋትና የቴክኖሎጂ አቅርቦትንና ሌሎች የስራ ቦታ ሁኔታዎችን ማሻሻል | አስተማማኝ አቅም ያለዉ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም |

# ክፍል 8

## 8. ዕይታዎች (Perspectives)

ዕይታዎች የአንድን ተቋም አፈፃፀም ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር ለማየት የሚያስችሉ ሚዛናዊ ሌንሶች ሲሆኑ፣ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በዋነኛነት የሚከተሉት አራት ዕይታዎች ይኖሩታል፡፡

### ሀ. የተገልጋይ ዕይታ

ተቋሙ ዘመናዊው ኢኮኖሚ የሚጠይቀውን አስተማማኝና ወቅታዊ የስታቲስቲክስ መረጃ ለማመንጨት፣ ለማሠራጨትና የመረጃ አጠቃቀም አድማሱን ለማስፋት የሚያስችሉ የስታቲስቲክስ አሠራሮችን በማሻሻልና በማጎልበት፣ ተከታታይና ዘላቂ በሆነ መልኩ የተገልጋዮችን የመረጃ ፍላጎት በማሟላት ተቋማዊ ራዕዩን እንደሚያሳካ ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የተገልጋይ ዕይታ የተቋሙ አንዱና ዋንኛው ዕይታ ይሆናል፡፡

### ለ. የፋይናንስ ዕይታ

ተቋሙ የፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነትን በማሻሻል በአጠቃላይ መንግሥት ለስታቲስቲክስ ሥራ የሚመድበውን ቋሚ በጀትና ከልማት አጋሮች የሚገኘውን የበጀት ድጋፍ ፍሰት እንዲጨምር ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባሮችን በማከናወን፣ እንዲሁም የፋይናንስ አሠራር ሥርዓቱን በማሻሻልና ጠንካራ የውስጥ ኦዲትና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት ውጤታማ የፋይናንስ አጠቃቀምን በማስፈን ተቋማዊ ራዕዩን ያሳካል፡፡ በመሆኑም የፋይናንስ ዕይታ የተቋሙ ሌላኛው ዕይታ ይሆናል፡፡

### ሐ. የአሠራር ዕይታ

ተቋሙ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ዘመናዊ የስታቲስቲክስ አሠራር ሥርዓትን በመዘርጋትና በማጎልበት፣ እሴትን የማይጨምሩ የሥራ ፍሰትና አሠራሮችን በማስወገድ ጥራቱን የጠበቀ የመረጃ አቅርቦት አሠራርና ቁጥጥር ሥራዎችን በማጠናከር፣ ለጥናትና ምርመር ሥራዎች ተገቢውን ትኩረት በመስጠት፣ እንዲሁም የተገልጋዮችና የባለድርሻ አካላት ግንኙነት ሥራ አመራርን በማጠናከርና ሌሎችም የውስጥ አሠራር ሂደቶችን በማሻሻል ተቋማዊ ስትራቴጂክ ዕቅዱን ያሳካል፡፡ ይህንን ለማድረግም ለአሠራሩ መሻሻል መነሻና ግብአት የሚሆኑ ዓለም አቀፍ ደረጃና ተወዳዳሪ የሆኑ ሚቶዶሎጂዎችን የመጠቀምና በመረጃ መሰብሰብና ቅንብር የቴክኖሎጂና የሎጂስቲክስ አቅሙንና የሥራ ከባቢን የማሻሻል አሠራሮችን በመዘርጋት ዘመናዊና ዓለም-አቀፍ ዕውቅናና ተአማኒነት ያለው የስታቲስቲክስ መረጃ በማቅረብ ተቋማዊ ራዕዩን ያሳካል፡፡ ከዚህም አንፃር የውስጥ አሠራር ዕይታን በመጠቀም ስትራቴጂያዊ ውጤቱን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

### መ. የመማማርና እድገት ዕይታ

ይህ ዕይታ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ዕይታዎች ቁሳዊ /Tangible/ ወደ ሆነ ውጤት ለመለወጥ የሚያስችሉ አዕምሯዊና ረቂቅ /Intangible/ የሆኑ ተቋማዊ ሀብቶችን የሚያካትት የዕይታ መስክ ሲሆን፣ በተቋማችን የሠራተኞችን እውቀት፣ ክህሎትና

አመለካከት ከማሳደግ፣ ምቹ የሥራ ሁኔታዎችን ከማሟላት፣ በተቋም ደረጃ የፈፃሚዎችን የመወሰን አቅም /Empowerment/ ከማጎልበት፣ የቡድን አሠራርና የአመራር ብቃትን ከማሻሻል፣ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ጠቀሜታን ከማሳደግ የኤጀንሲውን ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት የሚያስችል ይሆናል፡፡

# ክፍል 9

## ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ስትራቴጂያዊ ግቦች

| ዕይታዎች | ተ.ቁ | የኤጀንሲው ስትራቴጂያዊ ግቦች |
|---|---|---|
| የተገልጋይ/ ባለድርሻ አካላት ዕይታ | 1 | በየዘርፉ የተሟሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በማቅረብ የተጠቃሚዎችን እርካታ ማሣደግ፣ |
| | 2 | ከማ.ስ.ኤ. ውጭ ያሉ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም አባል መ/ቤቶችን ስታቲስቲካዊ አሰራር ዕውቀትና ክህሎት ማሣደግ፣ |
| | 3 | የመረጃ ሰጪዎችንና ተጠቃሚዎችን የስታቲስቲክስ ግንዛቤ ማዳበር፣ |
| | | |
| የፋይናንስ ዕይታ | 4 | የበጀት/ ፈንድ አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሣደግ፣ |
| | 5 | ከልማት አጋሮች የሚገኝ ፈንድ (የገንዘብ ቴክኒክና ማቴሪያል) ድጋፍ ማሣደግ፣ |
| | | |
| የውስጥ አሠራር ዕይታ | 6 | የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም ስታቲስቲካዊ አሰራሮችንና ሜቶዶሎጂዎችን ማሻሻል፣ |
| | 7 | የዶክመንቴሽን ሥርዓትን ማሻሻል፣ |
| | 8 | የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም የመረጃ ጥራት ቁጥጥርን ማጎልበት፣ |
| | 9 | የስታቲስቲክስ ምርምርና ትንተና ሥራዎችን ማሻሻል፣ |
| | 10 | የመረጃ አሰባሰብና ቅንብር ስርዓትን ማሻሻል፣ |
| | | |
| የመማማርና ዕድገት ዕይታ | 11 | የሥራ ከባቢ ምቹነትን ማሻሻል፣ |
| | 12 | የመ/ቤቱን ሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ፣ |
| | 13 | የITን አጠቃቀም ማሣደግ፣ |

## የማ.ስ.ኤ ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ የስትራቴጂያዊ ግቦች መግለጫ (Objective Commentary)ና ውጤት

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 1 | በየዘርፉ የተሟሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በማቅረብ የተጠቃሚዎችን እርካታ ማሳደግ | • በኢኮኖሚያዊ በማህበራዊ እና ስነ-ህዝብ መስክ የሚታዩ የመረጃ ክፍተቶችን እና ዋና ዋና አመላካች መረጃዎችን (indicators) በማሟላት የተጠቃሚን እርካታ ማሳደግ::<br>• የጥናት ውጤቶች የሚሰራጩበት ወይም የሚወጡበትን ወቅት የሚያሳይ የጊዜ ሰሌዳ (Release Calendar) አዘጋጅቶ ማቅረብ፣<br>• ወቅታቸውን ጠብቀው ከተካሄዱ የናሙና ጥናቶችና ቆጠራዎች የተገኙ መረጃዎችን ማቅረብ፣<br>• ጥራታቸው የተሻሻለ የኢኮኖሚ ፣የማህበራዊ እና የስነ-ህዝብ መረጃዎችን ለተጠቃሚ ማቅረብ፣<br>• ሽፋናቸው ከተሻሻለ የቆጠራና የናሙና ጥናት የተገኙ መረጃችን ለተጠቃሚ ማቅረብ፣<br>• መረጃዎችን በተደራጀ መልክ ለአጠቃቀምና ለተጠቃሚው የሚደርሱበትን አሰራር (መረጃን User friendly በሆነ መልክ ለማቅረብ የሚያስችሉ የተለያየ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን እንደ ድረ-ገጽ(website) ENADA፣ Ethioinfo.፣Socio Economic Atlas፣ Country STAT የመሳሰሉትን) መጠቀም፣<br>• የመረጃ ክምችቱን በማሻሻል የተጠቃሚውን የመረጃ ፍላጎት ማርካት:: | • ተከታታይነታቸውን ጠብቀው የወጡ የቆጠራና የጥናቶች ውጤቶች፣<br>• የተለያየ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የተሰራጨ መረጃ፣<br>• በተዘጋጀው (Release Calendar) መሠረት የወጡ የቆጠራና የጥናት ውጤቶች፣<br>• በየዘርፉ ሽፋናቸው የተሟላ የቆጠራና የጥናት ውጤቶች፣<br>• ከአንድ መረጃ ቋት ወይም (One window shopping) የተገኙ መረጃዎች፣<br>• በየዘርፉ ተሟልተው በቀረቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የረካ ተጠቃሚ፣ |
| 2 | ከማ.ስ.ኤ ውጭ ያሉ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም አባል መ/ቤቶች ስታቲስቲካዊ አሰራር ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ ፣ | • በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም ውስጥ ያሉ አባል መ/ቤቶች አቅም ከመገንባት አንፃር ያላቸውን ፍላጎት ለይቶ ማወቅ::<br>• በፍላጎትና አቅርቦት መካከል ያለውን ልዩነት/ክፍተት በመለየት የሚሰጠውን የአቅም ግንባታ ሥራ ማሳደግ:: | • ደረጃውን በጠበቀ ስታቲስቲካዊ አሰራር የሰለጠኑ መ/ቤቶች፣<br>• በአገልግሎቱ/ በተሰጠው ስልጠና የረኩ አባል መ/ቤቶች |
| 3 | የመረጃ ሰጭዎችንና ተጠቃሚዎችን የስታቲስቲክስ ግንዛቤ ማዳበር | • ትክክለኛ ስታቲስቲካዊ መረጃ ለመስጠትም ሆነ ለመጠቀም ዝግጁ የሆነ ህብረተሰብ ለመፍጠር የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ማድረግ፣ | • ትክክለኛ መረጃ በመስጠትና በመጠቀም በኩል የተሻለ አመለካከት ያለው ህብረተሰብ፣ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
|---|---|---|---|
| | | • የኤጀንሲውና የክልሎችን መዋቅር በመጠቀም በገጠርና በከተማ የሚገኘውን መረጃ ሰጪ ህብረተሰብ ስለስታቲስቲክስ መረጃ ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲያገኝ ማድረግ፣<br>• በመገናኛ ብዙሃን እና የማህበረሰብ ሚዲያዎች የአምድና የአየር ጊዜ በመከራየት የሚቀርቡ የማስተማሪያ እና የማስተዋወቂያ ፕሮግራሞችን በተከታታይ በማካሄድ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣<br>• በአውደ ጥናት፣ ሴሚናሮች፣ ስልጠናዎች እና በልዩ ልዩ ሁኔታ (Events) ላይ ስታቲስቲክስን የማስተዋወቅና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ መስራት፣<br>• ከመረጃ ሰጭዎችና ተጠቃሚዎች ጋር ያለውን የጋራ የትብብር መድረክ ማጐልበት፣<br>• የመረጃ ተጠቃሚዎችን ፍላጎትና የመረጃ ክፍተቶችን ለማሟላት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት፣ | • በህብረተሰቡ ዘንድ የተፈጠረ የተሻለ የስታቲስቲክስ ግንዛቤ፣ |
| 4 | የበጀት /ፈንድ አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ፣ | • በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር /በመንግስት/ ፀድቆ ለተቋሙ የተደለደለ በጀትንና ከልማት አጋሮች የተገኘ ፈንድ በመደበኛ ስራና በዕቅድ ለተያዙ ሥራዎች በአግባቡ ተግባር ላይ እንዲውል ማድረግ፣<br>• ለተቋሙ በመንግስት የተደለደለ በጀትና ከልማት አጋሮች የተገኘውን ፈንድ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው ዘመናዊ የፋይናንስ አሰራር በመከተል የመንግስትን ሕግ፣ደንብ፣መመሪያና የአሰራር ማንዋሎች ጠብቆ ለታለመለት አላማ ስራ ላይ ለመዋሉ የተጠናከረ የውስጥ ቁጥጥር/ኦዲት በመዘርጋት ማረጋገጥ፣ | • በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ የዋለ በጀት፣<br>• በአግባቡ ጥቅም ላይ የዋለ ከልማት አጋሮች የተገኘ ፈንድ፣ |
| 5 | ከልማት አጋሮች የሚገኝ ፈንድ (የገንዘብ ቴክኒክና ማቴሪያል) ድጋፍ ማሳደግ፣ | • ከልማት አጋሮች ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የቴክኒክ፣የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፍ ማፈላለግ፣ | • ከልማት አጋሮች የተገኘ የቴክኒክ፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ድጋፍ፣ |
| 6 | በብሔራዊ የስታቲስቲክስ ሲስተም | • በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም አባል መ/ቤቶች ውስጥ | • በሴክተር መ/ቤቶች ውስጥ የስታቲስቲክስ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
|---|---|---|---|
| | ውስጥ ስታቲስቲካዊ አሠራሮችንና ሜቶዶሎጂዎችን ማሻሻል፣ | የስታቲስቲክስ ዩኒት እንዲቋቋም ማድረግና በሙያው በሰለጠነ የሰው ኃይል እንዲደራጅ ማድረግ፣<br>• ወጥ የሆኑ አሰራሮችን በመዘርጋት ፅንሰ ሀሳቦችንና ፍቺዎችን፣ ምደባዎችን፣ ኮዶችን፣ ፎርማቶችን፣ ደረጃዎችንና የአሰራር ዘዴዎችን (Methodology) በማዘጋጀት ለጥናቶችና ለአስተዳደራዊ መዛግብት መረጃዎች አሰባሰቦ በግብዓትነት መጠቀም፣<br>• የመረጃ አያያዝ ስርዓትን (Data Management) ማጠናከር፣<br>• ሊቀናጁ የሚገባቸውን ጥናቶች በማቀናጀት ወጭንና ጊዜን መቆጠብ፣ | ሥራን በባለቤትነት የሚከታተል በባለሙያ የተደራጀ አካል፣<br>• የተቀላጠፈ አሰራር ፣<br>• አስተማማኝ፣ ተነፃፃሪና ጥራት ያለው መረጃ<br>• የተደራጀና ዘመናዊ የሆነ የስታቲስቲክስ መረጃ አሰባሰብና አያያዝ ዘዴ፣<br>• በተቀናጀ ሁኔታ ከተካሄዱ ጥናቶች የተገኙ ውጤቶች፣ |
| 7 | የዶክመንቴሽን ስርዓትን ማሻሻል፣ | • ተቋሙ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ያሉ የህትመት ኦዲዮቪዢዋል እና የፎቶግራፍ፣ የማቋቋሚያ አዋጆችን፣ ደንቦችን በቤተመፃህፍትና በሌሎች ያሉ መሰል የመረጃ ምንጮችን በማሰባሰብ እና በማቀነባበር የመስሪያ ቤቱን አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳይ (Profile) ደረጃውን የጠበቀ የዶክመንቴሽን ስርዓት መዘርጋት::<br>• ተቋሙ የሚያከናውናቸውን ቆጠራዎች እና የናሙና ጥናቶች የአሰራር ሂደት፣ የተሳተፉ ባለሙያዎች ብዛት እና ስብጥር፣ የተሳተፉ ባለድርሻ አካላት ብዛትና ስብጥር፣ በስራ ላይ የዋለ የሀብት መጠን፣ ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ የመፍትሄ ዕርምጃዎች የተገኙ መልካም ተሞክሮዎችን ...ወዘተ የሚያሳዩ ሰነዶች እና ኦዲዩቪዥዋል መረጃዎች በቋሚነት ማዘጋጀት::<br>• ተቋሙን አስመልክቶ የተሰጡ ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ ስልጠናዎች፣ የመስክ ስራዎች፣ ልምድ ልውውጦች፣ የአውደ ጥናቶች (Work Shop) አውደ ርዕይ(Exhibition) የመ/ቤቱን ማህበራዊ እና የመዝናኛ ፕሮግራሞች በአግባቡ ተቀርፀው በተለይ ለማስተዋወቅ ስራ በሚያመች መልኩ ማደራጀት:: | • ደረጃውን የጠበቀ ዘመናዊ የዶክመንቴሽን ስርዓት፣<br>• መስሪያ ቤቱን የሚያስተዋውቅና ለተጠቃሚ በሚያመች መልኩ የተዘጋጀ መግለጫ (Profile) |


| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
|---|---|---|---|
| | | • የተለያዩ ሰነዶች (የማኑዋሎች ፣የመጠይቆች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ የስታተስቲክስ ሪፖርቶችና የመፅሄቶች ኮፒዎች፣ካሴቶች ሲዲዎች....ወዘተ) በአግባቡና በጥንቃቄ ማከማቸት::<br>• ቋሚና ተከታታይነት ያለው የዶክመንቴሽን ስርዓትን የማሻሻል ስራ መስራት:: | |
| 8 | በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም ውስጥ የመረጃ ጥራት ቁጥጥርን ማጎልበት | • በተዘጋጀው የመረጃ ጥራት ማረጋገጫ መስፈርት (Data quality Assessment frame) መሰረት በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም የሚወጡ መረጃዎች በመገምገም ጥራታቸውን ማረጋገጥ::<br>• በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም አባላት የሚወጡ መረጃዎች አይነትና የሚወጡበትን ጊዜ (Release Calendar..ወዘተ ያካተተ የጋራ መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) መፈራረምና አፈፃፀሙን መከታተል::<br>• በስራ ላይ ላለው የስታተቲስቲክስ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ አዋጁ ማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብና አፈፃፀሙን መከታተል:: | • ጥራት ያለው ኦፊሻል ስታቲስቲክስ፣<br>• የተጣጣሙ የስታቲስቲክስ መረጃዎች፣<br>• የመረጃ ድግግሞሽ (Duplication efforts) የማይታይባቸው የስታቲስቲክስ ጥናት ውጤቶች፣<br>• ወጥ በሆነ ፅንሰ ሃሳቦችና ፍችዎቻቸው የሚጠቀሙ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ አባላት<br>• ጊዜያቸውን ጠብቀው የወጡ መረጃዎች |
| 9 | የስታቲስቲክስ ምርምርና ትንተና ሥራዎችን ማሻሻል፣ | • መ/ቤቱ ከሚያካሂዳቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች መረጃ ላይ ጥልቅ ትንተና ማከናወን፣<br>• ከጥልቅ ትንተናዎች የተገኙ ውጤቶችን፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን ለማሻሻል፣ በሚሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ የሚኖሩ ጉድለቶችን ለመለየት፣የግመታ ዘዴዎችን ለማሻሻል እና የተሻሻሉ አሠራሮችንና ሞዴሎችን ለማስገኘት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ::<br>• አዲስና የተሻሻሉ ሞዴሎች እና የግመታ ዘዴዎች ላይ ምርምር በማድረግና በመፈተሽ ተግባራዊ ማድረግ፣<br>• አዳዲስ ወይም የተሻሻሉ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴዎችን፣ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና የመስክ ቁጥጥር አሰራሮች በመፈተሽ ስራ ላይ ማዋል፣ | • ጥልቅ ትንተና የተሰራላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች፣<br>• ፍተሻ የተካሄደባቸው ሞዴሎች አሰራሮችና የግመታ ዘዴዎች፣<br>• ለሥራ ዝግጁ የሆኑ አዳዲስ የግመታ ዘዴዎች፣ሞዴሎች፣ ወዘተ. |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 10 | የመረጃ አሰባሰብ እና ቅንብር ስርዓትን ማሻሻል | • ለጥናቶችና ቆጠራዎች የቅድመ ዝግጅት ስራዎች፣ የመጠይቅ ዝግጅት፣የመረጃ ሰብሳቢ እና የተቆጣጣሪ መመሪያ፣የኤዲቲንግ እና ኮዲንግ መመሪያ፣ የታቡሌሽን ፕላንና ኤዲት ስፔስፊኬሽን፣ዝግጅትና የህትመት ስራዎች አሰራር ማጠናከር::<br>• የመረጃ አሰባሰብ ሂደትን የሚያፋጥኑ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንደ PDA፣ GPS፣ Ultra Portable device የመሳሰሉትን በመጠቀም የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት ማሻሻል::<br>• ጥሬ መረጃን ለማጠናቀርና ለመተንተን በተለይ cleaning፣ consistency check ፣ የሰንጠረዥ እና የሪፖርት ዝግጅት ስራዎችን ሊያፋጥኑ በሚችሉ ዘመናዊ Soft ware በመጠቀም የአሰራር ስርዓትን ማጠናከር::<br>• የመስክ ሰራተኞች የስልጠና አሰጣጥን በቪዲዮ ኮንፈረንስ የማድረግ ሒደትን ከወረዳ ኔት ወርክ ፕሮግራም ጋር በማቀናጀት፤ ወጪ ቆጣቢና ወጥ የሆነ ስልጠና በመስጠት Non- sampling error የሚቀንስ ዘመናዊ የአሰለጣጠን ዘዴን ማጠናከር እንዲሁም እያንዳንዱ ሰልጣኝ ስለጥናቱ በቂ ግንዛቤ ማግኘቱን መፈተሽ::<br>• ከዋናው መ/ቤት እስከ ቅ/ጽ/ቤት በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የመረጃ አሰባሰብ ጥራትን በእጅጉ የሚያጎለብቱ የመስክ ክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን ማጠናከር፣<br>• ኔት ወርክን በመጠቀም የዋናው መ/ቤት እና የቅ/ጽ/ቤት ግንኙነት ከመረጃ አሰባሰብ እስከ መረጃ ወደ ኮምፒውተር ማስገባት ያለው ስራ በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ የሚከናወንበት እና በNet work አማካኝነት መረጃን የመለዋወጥ ተግባር ማጠናከር::<br>• ስልጠናዎችን በመስጠትና ወጥ አሰራር በመዘርጋት በአስተዳደራዊ መዛግብት ያለውን የመረጃ ክፍተት ማሟላት:: | • የተደራጀ ዘመናዊ የአሰራር ስልጠና የወሰደ የመስክ ሰራተኛ ስልጠና<br>• ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች<br>• ዘመናዊና የተቀላጠፈ የመረጃ አሰባሰብና ቅንብር ስርአት<br>• ጥራቱን የጠበቀ ወቅታዊ መረጃ<br>• የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ<br>• በወቅቱ የተጠናቀቁ የስታቲስቲክስ ሪፖርቶች፣<br>• ጥራቱን የጠበቀ የተሟላ ወቅታዊ መረጃ፣ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 11 | የሥራ ከባቢ ምቹነትን ማሻሻል | • ሰራተኛው እንደሥራው ባሕሪ የተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ እየሰራ አዳዲስ ሐሳቦችን በማፍለቅ ሥራዎች ለማከናወን የሚያስችለውን ዘመናዊ የቢሮ አደረጃጀትና የተሟላ የሎጂስቲክ አቅርቦትና የስልጠና ቦታዎች ማመቻቸት::<br>• ከፍተኛ የሥራ ተነሳሽነት ያላቸው ሠራተኞች ለማፍራት ሠራተኛው በሥራ ውጤቱ ተጠቃሚ የሚሆንበት አሰራር ማጎልበት::<br>• የተሻለ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው ባለሙያዎች ለመቅጠር እንዲያስችል የቅጥር ስትራቴጂን ማሻሻል::<br>• በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የቅጥር፣ የደረጃ ዕድገት፣ የዝውውር አሰራሮችን ማሻሻል:: በአጠቃላይ መልካም አስተዳደርና ችሎታን (MERIT) ያማከለ አሰራርን ማስፈን::<br>• የቢሮና የመስክ ስራውን ለማቀላጠፍ እንዲቻል የተሽከርካሪም ሆነ ሌሎች የስራ መገልገያ መሳሪያዎች(ፋክስ፣ፕሪንተር፣ኮምፒውተር፣ፎቶኮፒ ማሽን፣ የህትመት ማሽኖች...ወዘተ) በወቅቱ ተጠግነው እንዲቀርቡ ማድረግ::<br>• የተቀላጠፈና ውጤታማ የዕቃ ግዢ አቅርቦት ስርዓት መዘርጋትና አፈፃፀሙን መከታተል:: | • በሥራ ውጤታቸው ተጠቃሚ የሆኑ ተነሳሽነት ያላቸው ሠራተኞች፣<br>• የተሻለ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸው አዲስ ቅጥር ሠራተኞች፣<br>• ግልፅነትና ተጠያቂነት ያለው በዕቅድ ላይ የተመሰረተ ቅጥር፣ ዕድገትና ዝውውር፣<br>• በአገልግሎት የረኩ ሠራተኞች፣<br>• የተሟላ እና ምቹ የስራ ቦታ፣<br>• ወቅቱን የጠበቀ ውጤታማ የዕቃ ግዥና ጥገና፣ |
| 12 | የመ/ቤቱን ሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ፣ | • የመ/ቤቱን ሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ለማሳደግ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ስልጠና ማመቻቸት፣<br>• የመ/ቤቱ ሠራተኞች የልምድ ልውውጥና የሥራ ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ::<br>• ሰራተኛው (የመስክ ሰራተኛውን ጭምር) ስለ ኤች.አይ.ቪ፣ ስርዓተ ፆታ፣ ስነ - ምግባርና ኮሚዩኒኬሽን ተከታታይ እውቀት የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ | • በሙያው የሰለጠነ በቂ የሰው ሀይል፣ |

| ተ.ቁ | ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ይዘትና ወሰን | ከግቡ የሚጠበቀው ውጤት |
|---|---|---|---|
| 13 | የIT ን አጠቃቀም ማሳደግ፣ | • አስተማማኝና ዘላቂ የሆነ የኔት ወርክ አገልግሎት በዋናው መ/ቤትና በቅ/ጽ/ቤቶች እንዲኖር ማድረግ፣<br>• የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለተጠቃሚው በ Geospatial መልክ ማቅረብ፣<br>• ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም መረጃ አሰባሰቡንና ቁጥጥሩን ማቀላጠፍ፣ | • አመቺና ግልፅ በሆነ መልኩ ለተጠቃሚ የቀረበ መረጃ፣<br>• አስተማማኝና ቀልጣፋ የሆነ የመረጃ መረብ አገልግሎት፣<br>• የተቀላጠፈ የመስክ ቁጥጥር ስራ፣ |

# የኤጀንሲው ስትራቴጂ ማፕ



# የማ.ስ.ኤ. የትኩረት መስክ የመለኪያዎች መግለጫ

| ተ.ቁ | መለኪያው የተቀረፀበት ግብ | የመለኪያው መጠሪያ | ቀመር | የቀመሩ መግለጫ | መስፈሪያ | የመረጃ ምንጭ | መረጃው የሚሰበሰብበት/ ሪፖርት የሚደረግበት/ ድግግሞሽ | መረጃውን የተነተነው/ት ክክለኛነቱን ያረጋገጠው |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| 1 | በየዘርፉ የተሟሉ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን በማቅረብ የተጠቃሚዎችን እርካታ ማሳደግ | • ተከታታይነታቸውን ጠብቀው (Periodicity) የወጡ የጥናቶችና የቆጠራ ውጤቶች በመቶኛ | • (ተከታታይነታቸውን ጠብቀው የወጡ የጥናትና ቆጠራ ውጤቶችx100 በዓመቱ የታቀዱ የጥናትና ቆጠራ ውጤቶች) | • ተከታታይነታቸውን ጠብቀው ይወጣሉ ተብለው ከታቀዱ ጥናቶችና ቆጠራዎች ምን ያህሉ በታቀደላቸው ጊዜ ተካሄዱ | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በዓመት | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት |
| | | • የሚሰራጩበት የጊዜ ሰሌዳ (Release Calendar) ጠብቀው የቀረቡ የጥናትና የቆጠራ ውጤቶች በመቶኛ | • (ወቅታቸውን ጠብቀው) የቀረቡ የጥናት የቆጠራ ውጤቶችX100/ ለማቅረብ የታቀዱ ጠቅላላ የጥናትና ቆጠራ ውጤቶች ብዛት) | • ወቅታቸውን ጠብቀው የወጡ ጥናትና ቆጠራ ውጤቶችን ሲወጡ ከታቀዱት ጋር በማነፃፀር ይሰላል | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በዓመት | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት |
| | | • በየዘርፉ የመረጃ ክፍተት እንዳላቸው ለተለዩ የጥናት ዓይነቶች መረጃ የቀረበላቸው ብዛት፣ | • በዓመቱ የተሰሩ data gap ያላቸው ጥናቶች ብዛት | • በዓመቱ የተሰሩ data gap ያላቸው ጥናቶች ብዛት ያመለክታል | በቁጥር | ማ.ስ.ኤ | በዓመት | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት/ ወሳኝ የስራ ሂደቶች |
| | | • በየዘርፉ ተሟልተው በቀረቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የተጠቃሚ እርካታ በመቶኛ | • (በመረጃው አቅርቦት የረኩ ተጠቃሚዎች ብዛት X 100 አጠቃላይ መጠይቁን የሞሉ ተጠቃሚዎች) | • በየዘርፉ ተሟልተው በቀረቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የረኩ ተጠቃሚዎችን አጠቃላይ መጠይቁን ከሞሉ ተጠቃሚዎች በማነጻፀር፣ | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በዓመት | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት/ የብሔራዊ ስታ. ጥራትና ደረጃዎች ዳሬክቶሬት |
| 2 | ከማስኤ ውጭ ያሉ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም አባል መ/ቤቶችን ስታቲስቲካዊ አሰራር ዕውቀትና ክህሎትን | • የስልጣኝ መ/ቤቶች እርካታ በመቶኛ | • በሥልጠና የረኩ ሰልጣኝ መ/ቤቶች ብዛትX 100 ጠቅላላ በስልጠናው የተሳተፉ የመ/ቤቶች ብዛት | • በየጊዜው ከሚሰራጭ ሰልጣኝ እርካታ መለኪያ መጠይቅን መሰረት ያደረገ | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በዓመት ሁለት ጊዜ | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት/ ብሔራዊ ስታ. ጥራትና ደረጃዎ ዳይሬክቶሬት |

| ተ.ቁ | መስኪያው የተቀረፀበት ግብ | የመስኪያው መጠሪያ | ቀመር | የቀመሩ መግለጫ | መስፈሪያ | የመረጃ ምንጭ | መረጃው የሚሰበሰብበት/ ሪፖርት የሚደረግበት/ ድግግሞሽ | መረጃውን የተነተነው/ት ክክለኛነቱን ያረጋገጠው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ማሳደግ | • የተሰጡ ስልጠናዎች ብዛት በመቶኛ | • ለአባል መ/ቤቶች የተሰጡ ሥልጠናዎች <u>ብዛት X 100</u> በዓመቱ ለአባል መ/ቤቶች ሊሰጡ የታቀዱ ስልጠናዎች | በዓመቱ አባል መ/ቤቶች የወሰዱአቸው ስልጠናዎችና ሊሰጡ የታቀዱ ስልጠናዎች ጋር በማነፃፀር የሚሰላ | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በዓመት አንድ ጊዜ | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራ ዳይሬክቶሬት/ ብሔራዊ ስታ. ጥራትና ደረጃዎ ዳይሬክቶሬት |
| 3 | የመረጃ ሰጪዎችንና ተጠቃሚዎችን የስታስቲክስ ግንዛቤ ማዳበር | • የስታቲስቲክስ ጥቅምን የሚያስገነዝቡ የሚዲያ መግለጫዎች ብዛት በመቶኛ | • ለሚዲያ መግለጫ የተዘጋጀላቸው ፕሮግራሞች <u>ብዛትX100</u> ለሚዲያ መግለጫ ሊዘጋጅላቸው የሚገቡ ፕሮግራሞች ብዛት | • ለሚዲያ መግለጫ የተዘጋጀላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች እና ፕሮግራሞች ብዛት ከጠቅላላው ለሚዲያ መግለጫ ቢዘጋጅላቸው ፕሮግራም ብዛት ጋር በማነፃፀር የተሰላ | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየሩብ ዓመቱ | የህዝብግንኙነት፣ ሕትመትና መረጃ ስርጭት ዳይሬክቶሬት |
| | | • የስታቲስቲክስን ጥቅም የሚያስገነዝቡ ፅሁፎች ብዛት | • ለህብረተሰቡ የተሰራጩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ፅሁፎች ብዛት | • የህብረተሰቡን ግንዛቤ ያዳብራል ተብለው የተዘጋጁ ፖስተር፣ መፅሔት፣በራሪ ፅሁፎች እና የመሳሰሉ የፅሁፍ አይነቶች መሰራጨታቸውን ያመለክታል:: | ቁጥር | ማ.ስ.ኤ | በየ6 ወሩ | የህዝብግንኙነት፣ ሕትመትና መረጃ ስርጭት ዳይሬክቶሬት |
| | | • በግብረ መልስ የተገኘ የተገልጋዮች ግንዛቤ በመቶኛ | • ግንዛቤ ማግኘታቸውን የገለፁ ተገልጋዮች <u>ብዛትX100</u> ለግብረ መልስ ጥናቱን መልስ የሰጡ ተገልጋዮች | • ግንዛቤ ማግኘታቸውን የገለፁ ተጠቃሚዎች የመጠይቁን ምላሽ ከሰጡት ጋር በማነፃፀር የሚሰላ ይሆናል:: | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በዓመት አንድ ጊዜ | የህዝብግንኙነት፣ ሕትመትና መረጃ ስርጭት ዳይሬክቶሬ |
| | | • ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር የጋራ ውይይት የተደረገባቸው በማ.ስ.ኤ የሚሰሩ ጥናቶች ብዛት በመቶኛ | • ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር ውይይት የተደረገባቸው የማ.ስ.ኤ ጥናቶች <u>ብዛትx100</u> በዓመቱ የተካሄዱ የማ.ስ.ኤ ጠቅላላ ጥናቶች ብዛት | • በዓመቱ በማ.ስ.ኤ ከተካሄዱ ጠቅላላ ጥናቶች መካከል ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር ውይይት የተካሄደባቸውን ጥናቶች ብዛት በማነፃፀር | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ጥራትናደረጃዎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት/ ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር |

| ተ.ቁ | መለኪያው የተቀረፀበት ግብ | የመለኪያው መጠሪያ | ቀመር | የቀመሩ መግለጫ | መስፈሪያ | የመረጃ ምንጭ | መረጃው የሚሰበሰብበት/ ሪፖርት የሚደረግበት/ ድግግሞሽ | መረጃውን የተነተነው/ት ክክለኛነቱን ያረጋገጠው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4 | የበጀት/ፈንድ አጠቃቀምና ውጤታማነትን ማሳደግ | • በወቅቱ ተጠናቅቆ የቀረበ የፋይናንስ ሪፖርት በመቶኛ | • በየወሩ ወቅታቸውን ጠብቀው የወጡ ወርሃዊ <u>የሂሳብ ሪፖርቶች X100</u> በየወሩ መቅረብ የነበረባቸው ወርሃዊ የሂሳብ ሪፖርቶች | • ወቅታቸውን ጠብቀው የወጡ የሂሳብ ሪፖርቶች በዕቅድ ከተያዙት የሂሳብ ሪፖርቶች ጋር በማነፃፀር የሚሰላ ይሆናል፣ | በመቶኛ | ግዥና ፋይናንስ | በዓመት 2 ጊዜ | ዳይሬክቶሬት<br>የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት |
| | | • በጀት/ ፈንድ ክንውን በመቶኛ | • የበጀት/ፈንድ <u>ክንውን X100</u> የበጀት/ ፈንድ ዕቅድ | • በወጪ በጀት የተከናወኑ ዕቅዶችን በወጭ በጀት እንዲከናወኑ ከታቀዱት ጠቅላላ ዕቅዶች በማነፃፀር የተሰላ | በመቶኛ | ማስኤ | በየዓመቱ | የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት |
| | | • ደንብ፣ መመሪያና ሕጐች ጠብቆ ለታለመለት አላማ ስራ ላይ የዋለ በጀት/ ፈንድ በመቶኛ | • የፋይናንስ መመሪያ ደንብና አዋጅን ተከትሎ ለታለመለት ዓላማ ስራላይ ስለመዋሉ ማረጋገጫ የተሰጠባቸው <u>የኦዲት ሪፖርቶች X 100</u> በአግባቡ ስራላይ ስለመዋሉ ለማረጋገጥ በውጭና በውስጥ ኦዲተሮች ከተደረጉ ጠቅላላ የኦዲት ስራዎች/ ምርመራዎች ብዛት | • ከተወሰኑ የሂሳብ ማስተካከያዎች በስተቀር በጀቱ/ፈንዱ ለታለመለት ዓላማ በአግባቡ ስራ ላይ ስለመዋሉ ማረጋገጫ የተሠጠበት የኦዲት ሪፖርት በጠቅላላ ከቀረቡ የኦዲት ሪፖርቶች ብዛት | በመቶኛ | ግዥና ፋይናንስ | በየዓመቱ | የግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት |
| | | • በኦዲት ፕሮግራም መሠረት የተሠራ የኦዲት ምርመራ በመቶኛ | • ምርመራቸው የተጠናቀቀ የዋናው መ/ቤት/ቅርንጫፍ <u>ጽ/ቤቶች ሂሳብ X100</u> ሂሳባቸው እንዲመረመር በዕቅድ ከተያዘው የዋናው መ/ቤት ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት | • የኦዲት ምርመራ የተደረገባቸው የቅ/ጽ/ቤቶች እና የዋናው መ/ቤት የኦዲት ስራ ብዛት በአጠቃላይ ለመመርመር በዕቅድ ከተያዘው ጋር ሲነፃፀር | በመቶኛ | ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት | በዓመት 2 ጊዜ | ኦዲትና ኢንስፔክሽ |
| | | • በወቅቱ የተጠናቀቀ የኦዲት ሪፖርት | • ወቅታቸውን ጠብቀው የወጡ የኦዲት <u>ሪፖርቶች X 100</u> ወቅቸውን ጠብቀው ይወጣሉ ተብለው በዕቅድ ከተያዙት የኦዲት ሪፖርቶች ብዛት | • ወቅታቸውን ጠብቀው የወጡ የኦዲት ሪፖርቶች በአጠቃላይ የኦዲት ሪፖርት ይወጣሉ ተብለው በዕቅድ ከተያዙት ጋር በማነፃፀር፣ | በመቶኛ | ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት | በዓመት 2 ጊዜ | ኦዲትና ኢንስፔክሽን ዳይሬክቶሬት |

| ተ.ቁ | መለኪያው የተቀረፀበት ግብ | የመለኪያው መጠሪያ | ቀመር | የቀመሩ መግለጫ | መስፈሪያ | የመረጃ ምንጭ | መረጃው የሚሰበሰብበት/ ሪፖርት የሚደረግበት/ ድግግሞሽ | መረጃውን የተነተነው/ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ከልማት አጋሮች የሚገኝ ፈንድ (የገንዘብ፣ቴክኒክና ማቴሪያል) ድጋፍ ማሳደግ | • ከልማት አጋሮች የተገኘ ፈንድ መጠን በመቶኛ | • ከልማት አጋሮች የተገኘ <u>የፈንድ መጠን X100</u><br>ከልማት አጋሮች ሊገኝ የታቀደ የፈንድ መጠን | • ከልማት አጋሮችየተገኘ የፈንድ መጠን ከጠቅላላው ከልማት አጋሮች ሊገኝ ከታቀደው የፈንድ መጠን ጋር በማነፃፀር የሚሰላ | መቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | /ብሔራዊ/ስታ. ጥራትና ደረጃዎች/ ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር ግኙና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት |
| 6 | የብሔራዊ ስታስቲክስ ሲስተም የስታቲስቲክስ አሰራሮችንና ሜቶዶሎጂዎችን ማሻሻል | • ወጥ የሆኑ አሰራሮችን የሚጠቀሙ መ/ቤቶች ብዛት በመቶኛ | • ወጥ የሆነ አሰራርን ለመተግበር (MOU) የፈረሙ አባል <u>መ/ቤቶች X100</u><br>ወጥ አሰራርን ለመተግበር (MOU) እንዲፈርሙ የታቀዱ መ/ቤቶች | • ወጥ የሆነ አሰራርን ለመተግበር(MOU) የፈረሙ አባል መ/ቤቶች ብዛት ወጥ የሆነ አሰራርን ለመተግበር (MOU) እንዲፈርሙ የታቀዱ መ/ቤቶችን በማነፃጸር የተሰላ:: | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ብሔራዊ ስታቲስቲክስ ጥራትና ደረጃዎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት |
| | | • የተቀናጁ ጥናቶች ብዛት በመቶኛ | • የተቀናጁ ጥናቶች <u>ብዛት X 100</u><br>መቀናጀትየሚገባቸው ጥናቶች ብዛት | • የተቀናጁ ጥናቶች ብዛት መቀናጀት ከሚገባቸው ጥናቶች ብዛት ጋር በማነፃፀር የሚሰላ ነው | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ብሔራዊ የስታስቲክስ ጥራትና ደረጃዎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት |
| | | • በማስኤ የተዘጋጁ ወጥ አሰራሮች በመቶኛ | • በማስኤ የተዘጋጁ ወጥ <u>አሰራሮችX100</u><br>በማስኤ ታቅደው ሊዘጋጁ የሚገባቸው ወጥ አሰራሮች | • በማስኤ ሊዘጋጁ የሚገባቸው ወጥ ፅንሰ ሃሳቦችና ፍቺዎቻቸው ኮዶችና ምደባዎችን ይመለከታል | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ብሔራዊ የስታስቲክስ ጥራትና ደረጃዎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት |
| 7 | የዶክመንቴሽን ስርዓትን ማሻሻል | • በዶክመንቴሽን ስርዓቱ የተካተቱ ዶክመንቶች ብዛት በመቶኛ | • በስርዓቱ የተካተቱ የዶክመንቴሽን <u>መረጃዎች ብዛት X 100</u><br>አጠቃላይ ሊሰበሰቡ የሚገባቸው የዶክመንቶች ብዛት | • ተቋሙ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮየተጠቀመባቸውና ያለፈባቸውን ታሪክ የያዙ ልዩ ልዩ ሰነዶች፣ መረጃዎች፣ገላጭናግልፅ በሆነ መስፈርት ዘመናዊ በሆነ ሁኔታ መካተታቸውን የሚያመላክት ይሆናል | በመቶኛ | • ማ.ስ.ኤ<br>• ታሪካዊ መረጃዎች የሚገኙባቸው ሌሎች መስሪያቤቶች<br>• ከሚመለከታቸው ግለሰቦች | በየስድስት ወሩ | የህዝብግንኙነት ህትመትና መረጃ ስርጭት ዳይሬክቶሬት |

| ተ.ቁ | መለኪያው የተቀረፀበት ግብ | የመለኪያው መጠሪያ | ቀመር | የቀመሩ መግለጫ | መስፈሪያ | የመረጃ ምንጭ | መረጃው የሚሰበሰብበት/ ሪፖርት የሚደረግበት/ ድግግሞሽ | መረጃውን የተነተነው/ት ክክለኛነቱን ያረጋገጠው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | በብሔራዊ ስታስቲክስ ሲስተም ውስጥ የመረጃ ጥራት ቁጥጥርን ማጎልበት | • የኦፊሻል ስታቲስቲክስ ብዛት በመቶኛ | • በማስኤ ግምገማ የተካሄደላቸው ጥናቶች ብዛት X 100 / የመረጃ ጥራት ማረጋገጫ ለማግኘት ጥያቄ የቀረበላቸዉ ጥናቶች ብዛት | • የመረጃ ጥራት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው ጥያቄ ከቀረረበባቸዉ ጥናቶች በማስኤ ግምገማ የተካሄደላቸው ጥናቶች ብዛት በመቶኛ ስሌት ነው:: | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ብሔራዊ የስታስቲክስ ጥራትና ደረጃዎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት |
| 9 | የስታቲስቲክስ ምርምርና ትንተና ሥራዎችን ማሻሻል | • ትንተና የተሰራላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች ብዛት | • ትንተና የተሰራላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች ብዛት | • ትንተና የተሰራላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች ይመለከታል | በቁጥር | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ወሳኝ የስራ ሂደቶች/ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር |
| | | • ጥልቅ ትንተና የተካሄደላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች ብዛት | • ጥልቅ ትንተና የተካሄደላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች ብዛት | • ጥልቅ ትንተና የተካሄደላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎችን ይመለከታል | በቁጥር | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ወሳኝ የስራ ሂደቶች/ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር |
| | | • ለሥራ ዝግጁ የሆኑ አዳዲስ/የተሻሻሉ የግመታ ዘዴዎች፣ ሞዴሎችና የአሠራር ስልቶች ብዛት | • ለስራ ዝግጁ የሆኑ አዳዲስ/ የተሻሻሉ የግመታ ዘዴዎች፣ ሞዴሎችና የአሠራር ስልቶች ብዛት | • ለስራ ዝግጁ የሆኑ አዳዲስ/ የተሻሻሉ የግመታ ዘዴዎች፣ ሞዴሎችና የአሠራር ስልቶችን ይመለከታል | በቁጥር | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ብሔራዊ የስታቲስቲክስ ጥራትና ደረጃዎች ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት |
| 10 | የመረጃ አሰባሰብና ቅንብር አሰራርን ማሻሻል | • የተደራጀ ዘመናዊ የመስክ ሠራተኞች ስልጠና ብዛት በመቶኛ | • በተደራጁና ዘመናዊ በሆነ መንገድ የተካሄደ ስልጠና ብዛትX100 / በአመቱ በአጠቃላይ የተካሄዱ ስልጠናዎች ብዛት | • በቪዲዮ ኮንፈረንስ፣ ዲቪዲ፣ ሲዲ የተሰጡ ስልጠናዎች፤በዓመቱ ከተካሄዱ ስልጠናዎች ብዛት ጋር በማነፃፀር የሚሰላ | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ወሳኝ የስር ሂደቶች/ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር |
| | | • ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በመቶኛ | • ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የዋለባቸው የቆ/ቦታዎች፣ የገበያ ቦታዎች...ወዘተX 100 / ለጥናቱ የተመረጡ ጠቅላላ የቆጠራ ቦታዎች ብዛት | • ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማለትም PDA፣GPS፣ Ultra portable device ወዘተ ጥቅም ላይ የዋለባቸው የቆ/ቦታዎች፣የገበያ ቦታዎች፣ኢንተርፕራይዝ ኢንዱስትሪ ወዘተ... አጠቃላይ ለጥናቱ የተመረጡ፣ የቆ/ቦታዎች የገበያ ቦታዎች ወዘተ.... | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ወሳኝ የስራ ሂደቶች |

| ተ.ቁ | መለኪያው የተቀረፀበት ግብ | የመለኪያው መጠሪያ | ቀመር | የቀመሩ መግለጫ | መለኪያ | የመረጃ ምንጭ | መረጃው የሚሰበሰብበት/ ሪፖርት የሚደረግበት/ ድግግሞሽ | መረጃውን የተነተነው/ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በማነፃፀር ይሰላል | | | | |
| | | • መረጃ በተሞላባቸው መጠይቆች ላይ የተገኙ ስህተቶች ብዛት በመቶኛ | • (በመጠይቆች ላይ የታዩ የስህተቶች ብዛት X 100 / አጠቃላይ የታዩ መጠይቆች ብዛት) | • በመስክ ቁጥጥርና በኤዲቲንግና ኮዲንግ ወቅት በመጠይቆች ላይ የታዩ የስህተቶች ብዛት ከአጠቃላይ በቁጥጥር ወቅት ከታዩ መጠይቆች ብዛት በማነፃፀር ይሰላል | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየጥናቱ ወቅት | ወሳኝ የስራ ሂደቶች/ቅ/ጽ/ቤቶች/የኤዲቲንግ ዳታ ኢንትሪና ኮምፒውተር ክሊኒንግ ማስተባበሪያ መምሪያ |
| | | • የተቀላጠፈ የመረጃ ቅንብር አሰራር በመቶኛ | • (እያንዳንዱ የስራ ዓይነት የፈጀበት ጊዜX100 / አጠቃላይ ለመጠናቀቅ የታቀደበት ጊዜ) | • ከኤዲቲንግ፣ ኮዲንግ፣ ዳታ ኢንትሪ፣ ቬሪፊኬሽን የዳታ Consistency check፣ የመረጃ ማቀናበር እና ትንተና ስራዎች የሚፈጁት ጊዜ፤ አጠቃላይ ሂደቱ ይፈጃል ተብሎ የወጣለት የጊዜ ገደብ ጋር በማነፃፀር ይሰላል | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ወሳኝ የስራ ሂደቶች/ቅ/ጽ/ቤቶች/የኤዲቲንግ ዳታ ኢንትሪና ኮምፒውተር ክሊኒንግ ማስተባበሪያ መምሪያ |
| | | • በወቅቱ የተጠናቀቀ የስታቲስቲክስ ሪፖርቶች ብዛት በመቶኛ | • (በተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ የተጠናቀቁ የስታቲስቲክስ ሪፖርቶች ብዛትX100 / አጠቃላይ ሊወጡ ከታቀዱ ሪፖርቶች ብዛት) | • በተዘጋጀው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የተጠናቀቁ/የስታቲስቲክስ ሪፖርቶች ብዛት ከአጠቃላይ ከታቀዱ ሪፖርቶች ብዛት በማነፃፀር የሚሰላ | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ወሳኝ የስራ ሂደቶች/እቅድና ለውጥ ሥራ አመራር |
| 11 | የስራ ከባቢ ምቹነት ማሻሻል | • የመ/ቤቱ ሰራተኞች እርካታ በመቶኛ | • በአገልግሎቱ የረኩ ብዛት X 100 / መጠይቁን የሞሉ የመ/ቤቱ ሰራተኞች ብዛት | • በአገልግሎቱ የረኩ ሰራተኞች ብዛት መጠይቁን ከሞሉት አንፃር ሲነፃፀር | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት/የሰው ሃብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት |
| | | • ከፍተኛ ደረጃ ያገኙ ዳይሬክቶሬቶችና/ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት | • የተሸለሙ ዳይሬክቶሬቶችና/ቅ/ጽ/ቤቶች | • የተሸለሙ ዳይሬክቶሬቶችና/ቅ/ጽ/ቤቶች ያመለክታል | በቁጥር | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር |

| ተ.ቁ | መለኪያው የተቀረፀበት ግብ | የመለኪያው መጠሪያ | ቀመር | የቀመሩ መግለጫ | መስፈሪያ | የመረጃ ምንጭ | መረጃው የሚሰበሰብበት/ ሪፖርት የሚደረግበት/ ድግግሞሽ | መረጃውን የተነተነው/ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | • ከቀረበው የሰው ሀይል ጥያቄ አንፃር የተሞሉ የሥራ መደቦች | • የተሞሉ የሥራ መደቦች ብዛትX100<br>በቀረበው ጥያቄ መሰረት እንዲሟላ የታቀደው የሰው ሃይል ብዛት | • ከእያንዳንዱ የስራ ሂደት ከቀረበው የሰው ሃይል ጥያቄ ጋር በማነፃፀር የሚሰላ | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ዕቅድና ለውጥ ሥራ አመራር/ የሰው ሃብት ሥራ አመራር |
| | | • በወቅቱ ገራዥ የገቡ መኪኖች ብዛት በመቶኛ | • በወቅቱ ጋራዥ የገቡ መኪኖች ብዛት X100<br>በወቅቱ ጥገና የተጠየቀላቸው መኪኖች ብዛት | • በወቅቱ ጥገና ከተጠየቀላቸው መኪኖች ውስጥ ገራዥ የገቡትን መኪኖች ብዛት ጋር በማነፃፀር ይሰላል | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየሩብ ዓመቱ | የጠቅላላ አገልግሎት ንብረትና ጥገና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የዴስክ ኃላፊዎች |
| | | • በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ (ሐምሌና ነሐሴ) ጥገና የተደረገላቸው መኪኖች ብዛት | • በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ለቅ/ጽ/ቤቶች ጥገና የተደረገላቸው መኪኖች ብዛትX100<br>በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከቅ/ጽ/ቤቶች የጥገና ጥያቄ የቀረበላቸው መኪኖች ብዛት | • በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ቅ/ጽ/ቤቶች የጥገና ጥያቄ ከቀረበላቸው መኪኖች ውስጥ ጥገና ከተደረገላው ጋር በማነፃፀር ይሰላል | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በዓመቱ | የጠቅላላ አገልግሎት ንብረትና ጥገና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት የዴስክ ኃላፊዎች |
| 12 | የመ/ቤቱን ሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ | • ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሠራተኞች ብዛት በመቶኛ | • ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሠራተኞች ብዛትx100<br>ጠቅላላ ሠራተኞች ብዛት | • 75 ከመቶ እና ከዚያ በላይ የስራ የአፈፃፀም ነጥብ ያስመዘገቡ ሠራተኞች ብዛት ከጠቅላላ ሠራተኞች ብዛት ጋር በማነፃፀር የሚሰራ ነው | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየ 6 ወሩ | የሰው ሀብት ልማት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት |
| | | • የተሰጡ ስልጠናዎች ብዛት በመቶኛ | • በአገር ውስጥ የተሰጡ ስልጠናዎች ብዛትx100<br>ሊሰጡ የታቀዱ ስልጠናዎች ብዛት | • በአገር ውስጥና በውጭ አገር አጭር፣ ረጅምና የስራ ላይ ስልጠናዎች ከታቀዱት ስልጠናዎች ጋር በማነፃፀር ይሰላል | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | የሰው ሀብት ልማት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት |
| | | | • በውጭ አገር የተሰጡ ስልጠናዎች ብዛትX 100<br>በዓመቱ ከውጭ ይገኛሉ ተብለው የታቀዱ ስልጠናዎች | • በውጭ አገር የተሰጡ አጭር እና ረጂም ስልጠናዎች ከታቀዱት ስልጠናዎች ጋር በማነፃፀር ይሰላል | በመቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | የሰው ሀብት ልማት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት |

| ተ.ቁ | መለኪያው የተቀረፀበት ግብ | የመለኪያው መጠሪያ | ቀመር | የቀመሩ መግለጫ | መስፈሪያ | የመረጃ ምንጭ | መረጃው የሚሰበሰብበት/ ሪፖርት የሚደረግበት/ ድግግሞሽ | መረጃውን የተነተነው/ት ክክለኛነቱን ያረጋገጠው |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 13 | የIT አጠቃቀምን ማሣደግ | • አስተማማኝ የኔት ወርክ አገልግሎት ያገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት በመቶኛ | • አስተማማኝ የኔት ወርክ አገልግሎት ያገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛትX100<br>ጠቅላላ መረጃ መረብ (Network) የተገናኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት | • አስተማማኝ የኔት ወርክ አገልግሎት ያገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ከጠቅላላ በኔትወርክ ከተገናኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ጋር በማነፃፀር የሚሰላ ነዉ፡፡ | መቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | የኢንፎርሜሽን ሲስተም ቴክኖሎጂ (IST) ዳይሬክቶሬት |
| | | • በጂኦ ስፓሻል መልክ መረጃ የወጣላቸው ጥናቶች ብዛት | • በዓመቱ በጂኦ ስፓሻል መልክ መረጃ ተዘጋጅቶላቸው የወጡ ጥናቶች ብዛት | • ገላጭ በሆነ መልኩ በጂኦ ስፓሻል መልክ ተዘጋጅተው የቀረቡ ጠቅላላ የጥናት ውጤቶችን ያመለክታል፡፡ | በቁጥር | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | ካርቶግራፊ እና GIS ዳይሬክቶሬት |
| | | • ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብና ቁጥጥር የሚያጐለብት ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ጥናቶች ብዛት | • በዓመቱ ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብና ቁጥጥር ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ጠቅላላ ጥናቶች ብዛት | • ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብና የቁጥጥር ቴክኖሎጂዎች እንደ PDA፣ GPS፣ UMPC፣…ወዘተ እና በሣተላይት ኢሜጀሪ የታገዙ ዲጂታል ካርታዎች የሚጠቀሙ ጥናቶች ብዛት | በቁጥር | ማ.ስ.ኤ | በየዓመቱ | IST/ካርቶግራፊ እና GIS ዳይሬክቶሬት |
| | | • የመ/ቤቱ የመረጃ መረብ መቋረጥ በመቶኛ | • የመረጃ መረቡ የተቋረጠባቸው የጊዜ መጠን X 100<br>ጠቅላላ የአገልግሎት መጠን | • የመረጃ መረቡ የተቋረጠበት የጊዜ መጠን ከጠቅላላ የአገልግሎት ጊዜ በማነፃፀር የተሰላ | መቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በየ 6 ወሩ | የኢንፎርሜሽን ሲስተም ቴክኖሎጂ (IST) ዳይሬክቶሬት |
| | | • በመ/ቤቱ የመረጃ ማሰራጫ ቴክኖሎጂ ላይ እርካታ ያገኙ ተጠቃሚዎችበመቶኛ | • (የማሰራጫ ቴክኖሎጂ ዘዴውን ተጠቅመው የረኩ ተጠቃሚዎችX 100<br>በአጠቃይ የማሰራጫውን ቴክኖሎጂ የተጠቀሙ ተጠቃሚዎች) | • መጠይቅ በማዘጋጀት መጠይቁን ከሞሉ ተጠቃሚዎች ምን ያህል በቴክኖሎጂው እርካታ (Satisfied) እንዳገኙ ያመለክታል | መቶኛ | ማ.ስ.ኤ | በዓመት | የኢንፎርሜሽን ሲስተም ቴክኖሎጂ (IST) ዳይሬክቶሬት |

# የማ.ስ.ኤ ስትራቴጂያዊ ዒላማዎች (Targets) መግለጫ

| ተ.ቁ. | ግብ | መለኪያ | የአፈጻጸም መነሻ Baseline | የዒላማ ምንጮች | የአፈጻጸም ደረጃዎች (Threshold) | | | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አረንጓዴ | ቢጫ | ቀይ | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
| 1 | በየዘርፉ የተሟሉ ስታቲስቲካዊ የመረጃዎችን በማቅረብ የተጠቃሚዎችን እርካታን ማሳደግ | - ተከታታይነታቸውን ጠብቀው (Periodicaity) የወጡ የጥናቶችና የቆጠራ ውጤቶች በመቶኛ | 50 | ማ.ስ.ኤ | >75 | 70-75 | <70 | 70 | 75 | 80 | 85 | 90 |
| | | - የሚሰራጩበት የጊዜ (Release Calander) ጠብቀው የቀረቡ የጥናትና የቆጠራ ውጤቶች በመቶኛ | 8 | ማ.ስ.ኤ | >15 | 8-15 | <8 | 8 | 12 | 20 | 30 | 40 |
| | | - በየዘርፉ የመረጃ ክፍተት እንዳላቸው ለተለዩ የጥናት ዓይነቶች መረጃ የቀረበላቸው ብዛት | - | ማ.ስ.ኤ | >1 | 1 | <0 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| | | - በየዘርፉ ተሟልተው በቀረቡ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች የተጠቃሚ እርካታ በመቶኛ | 50 | ማ.ስ.ኤ | >55 | 50-55 | <50 | 55 | 60 | 65 | 70 | 75 |
| 2 | ከማስኤ ውጭ ያሉ የብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም አባል መ/ቤቶችን ስታቲስቲካዊ አሰራር ዕውቀትና ክህሎትን ማሳደግ | - የሰልጣኝ መ/ቤቶች እርካታ በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >60 | 55-60 | <55 | - | 55 | 60 | 70 | 75 |
| | | - የተሰጡ ስልጠናዎች ብዛት | - | ማ.ስ.ኤ | >24 | 12-24 | <12 | - | 12 | 24 | 28 | 36 |
| 3 | የመረጃ ሰጪዎችና ተጠቃሚዎችን የስታቲስቲክስ ግንዛቤ ማዳበር | - የስታስቲክስ ጥቅምን የሚያስገነዝቡ የሚዲያ መግለጫዎች ብዛት በመቶኛ | 15 | ማ.ስ.ኤ | >35 | 25-35 | <25 | 25 | - | 45 | 60 | 70 |
| | | - የስታቲስቲክስን ጥቅም የሚያስገነዝቡ ፅሁፎች ብዛት በመቶኛ | 5 | ማ.ስ.ኤ | >10 | 7-10 | <7 | 7 | 10 | 12 | 12 | 15 |
| | | - ከግብረ መልስ የተገኘ የተገልዩች ግንዛቤ በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >25 | 20-15 | <20 | - | 25 | 30 | 40 | 50 |
| | | - ከመረጃ ተጠቃሚዎች ጋር ውይይት የተደረገባቸው በማ.ስ.ኤ | 50 | ማ.ስ.ኤ | >60 | 55-60 | <55 | 55 | 60 | 70 | 85 | 90 |

| ተ.ቁ. | ግብ | መለኪያ | የአፈጻጸም መነሻ Baseline | የዒላማ ምንጮች | የአፈጻጸም ደረጃዎች (Threshold) | | | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አረንጓዴ | ቢጫ | ቀይ | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
| | | የሚሰሩ ጥናቶች ብዛት በመቶኛ | | | | | | | | | | |
| 4 | የበጀት/ፈንድ አጠቃቀምና ውጤታማነትን ማሳደግ | - በወቅቱ ተጠናቶ የቀረበ የፋይናንስ ሪፖርት በመቶኛ | 18 | ማ.ስ.ኤ | >35 | 18-35 | <18 | 35 | 45 | 55 | 65 | 75 |
| | | - በጀት/ፈንድ ክንውን በመቶኛ | 92 | ማ.ስ.ኤ | >93 | 92-93 | <92 | 92 | 93 | 94 | 95 | 97 |
| | | - የፋይናንስ መመሪያ እና ደንብን ጠብቆ ለታለመለት አላማ ስራ ላይ የዋለ በጀት/ፈንድ በመቶኛ | 75 | ማ.ስ.ኤ | >78 | 70-78 | <78 | 75 | 78 | 80 | 85 | 90 |
| | | - በኦዲት ፕሮግራም መሰረት የተሠራ የኦዲት ምርመራ በመቶኛ | 71 | ማ.ስ.ኤ | >80 | 71-80 | <71 | 71 | 76 | 80 | 85 | 90 |
| | | - በወቅቱ የተጠናቀቀ የኦዲት ሪፖርት | - | ማ.ስ.ኤ | >50 | 40-50 | <40 | 40 | 45 | 50 | 55 | 60 |
| 5 | ክልማት አጋሮች የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ማሳደግ | - ክልማት አጋሮች የተገኘ ፈንድ መጠን በመቶኛ | 55 | ማ.ስ.ኤ | >65 | 60-65 | <60 | 60 | 65 | 70 | 80 | 90 |
| 6 | በብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሲስተም ውስጥ የስታቲስቲክስ አሰራሮችንና ሜቶዶሎጂዎችን ማሻሻል | - ወጥ የሆኑ አሰራሮችን የሚጠቀሙ መ/ቤቶች ብዛት በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >12 | 10-12 | <10 | 12 | 24 | 35 | 17 | 12 |
| | | - የተቀናጁ ጥቶች ብዛት በመቶኛ | 50 | ማ.ስ.ኤ | >55 | 50-55 | <50 | 55 | 60 | 65 | 70 | 75 |
| | | - በማስኤ የተዘጋጁ ወጥ አሰራሮች በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >25 | 13-25 | <13 | 37 | 25 | 25 | 13 | - |
| 7 | የዶክሜንቴሽን ስርዓትን ማሻሻል | - በዶክመንቴሽን ስርዓት የተካተቱ ዶክመንቶች ብዛት በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >25 | 10-25 | <10 | - | 10 | 25 | 35 | 50 |
| 8 | በብሔራዊ ስታስቲክስ ሲስተም ውስጥ የመረጃ ጥራት ቁጥጥር | - የኦፊሻል ስታቲስቲክስ ብዛት በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >55 | 50-55 | <50 | - | 50 | 50 | 55 | 60 |

| ተ.ቁ. | ግብ | መስኪያ | የአፈጻጸም መነሻ Baseline | የዒላማ ምንጮች | የአፈጻጸም ደረጃዎች (Threshold) | | | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አረንጓዴ | ቢጫ | ቀይ | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
| | ማገልበት | | | | | | | | | | | |
| 9 | የስታቲስቲካዊ ምርምርና ትንተና ሥራዎችን ማሻሻል | - ትንተና የተካሄደላቸው ጥናቶችና ቆጠራዎች ብዛት | 1 | ማ.ስ.ኤ | >2 | 1-2 | <1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 7 |
| | | - ጥልቅ ትንተና የተካሄደላቸው ጥናቶች ቆጠራዎች ብዛት | 2 | ማ.ስ.ኤ | >1 | 1 | <1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 |
| | | - ለሥራ ዝግጁ የሆኑ አዳዲስ/የተሻሻሉ የግመታ ዘዴዎች፣ ሞዴሎችና የአሠራር ስልቶች ብዛት | 1 | ማ.ስ.ኤ | 2 | 1 | 0 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 |
| 10 | የመረጃ አሰባሰብና ቅንብር ስርዓትን ማሻሻል | - የተደራጀ ዘመናዊ የመስክ ሠራተኞች ስልጠና ብዛት በመቶኛ | 1 | ማ.ስ.ኤ | >5 | 3-5 | <5 | 3* | 5* | 7* | 8* | 10* |
| | | - ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በመቶኛ | 28 | ማ.ስ.ኤ | >35 | 28-35 | <28 | 28 | 35 | 40 | 45 | 50 |
| | | - መረጃ በተሞላባቸው መጠይቆች ላይ የተገኙ ስህተቶች ብዛት በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | <30 | 30-35 | >35 | 35 | 30 | 25 | 15 | 10 |
| | | - የተቀላጠፈ የመረጃ ቅንብር አሰራር በመቶኛ | 130 | ማ.ስ.ኤ | ≤110 | 110-125 | >120 | 125 | 120 | 115 | 110 | 105 |
| | | - በወቅቱ የተጠናቀቁ የስታቲስቲክስ ሪፖርቶች ብዛት በመቶኛ | 55 | ማ.ስ.ኤ | >65 | 55-65 | <55 | 55 | 60 | 65 | 70 | 75 |
| 11 | የሥራ ከባቢ ምቹነትን ምሻሻል | - የመ/ቤቱ ሰራተኞች እርካታ በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >65 | 58-65 | <58 | 60 | 62 | 65 | 70 | 75 |
| | | - ከፍተኛ ደረጃ ያገኙ ዳይሬክተሮች/ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት | - | ማ.ስ.ኤ | >10 | 3-10 | <3 | 3 | 10 | 12 | 15 | 20 |
| | | - ከየዳይሬክተሩ/ቅ/ጽ/ቤቶች የተሸለሙ ሰራተኞች ብዛት | - | ማ.ስ.ኤ | >10 | 1-10 | <1 | - | 10 | 15 | 20 | 30 |
| | | - ከቀረበው የሰው ሃይል ጥያቄ አንፃር የተሞሉ የሥራ መደቦች | - | ማ.ስ.ኤ | >70 | 50 - 70 | <50 | 60 | 65 | 70 | 75 | 80 |

| ተ.ቁ. | ግብ | መለኪያ | የአፈጻጸም መነሻ Baseline | የዒላማ ምንጮች | የአፈጻጸም ደረጃዎች (Threshold) | | | ዒላማ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | አረንጓዴ | ቢጫ | ቀይ | 2003 | 2004 | 2005 | 2006 | 2007 |
| | | - በወቅቱ ገራዥ የገቡ መኪኖች ብዛት በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >65 | 60-65 | <60 | 60 | 65 | 70 | 75 | 80 |
| | | - በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ (ሐምሌና ነሐሴ) ጥገና የተደረገላቸው መኪኖች ብዛት በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >60 | 50-60 | <50 | 40 | 55 | 60 | 65 | 70 |
| 12 | የመ/ቤቱን ሠራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ | - ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሠራተኞች ብዛት በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >20 | 10-20 | <10 | - | 10 | 20 | 30 | 35 |
| | | - በአገር ውስጥ የተሰጡ ስልጠናዎች ብዛት በመቶኛ | 75 | ማ.ስ.ኤ | >85 | 80-85 | <80 | 80 | 85 | 90 | 95 | 95 |
| | | - በውጭ አገር የተሰጡ ስልጠናዎች በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >55 | 50-55 | <50 | - | 50 | 55 | 60 | 65 |
| 13 | የIT አጠቃቀምን ማሣደግ | - አስተማማኝ የኔትወርክ አገልግሎት ያገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ብዛት በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >70 | 65-70 | <70 | 70 | 75 | 80 | 85 | 90 |
| | | - በጂኦ ስፓሻል ዳታ መልክ መረጃ የወጣላቸው ጥናቶች ብዛት | 2 | ማ.ስ.ኤ | >3 | 2 | <1 | 3* | 3* | 1* | 1* | 3* |
| | | - ዘመናዊ የመረጃ አሰባሰብና ቁጥጥር የሚያጐለብት ቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ጥናቶች ብዛት | 2 | ማ.ስ.ኤ | >2 | 2 | <1 | 5* 3+2 | 5* 3+2 | 5* 2+3 | 7* 4+3 | 6* 2+4 |
| | | - የመ/ቤቱ የመረጃ መረብ መቋረጥ በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >60 | 60-65 | <60 | 60 | 65 | 70 | 80 | 90 |
| | | - በመ/ቤቱ የመረጃ ማሰራጫ ቴክኖሎጂ ላይ እርካታ ያገኙ ተጠቃሚዎች በመቶኛ | - | ማ.ስ.ኤ | >80 | 75-80 | <75 | 75 | 75 | 80 | 85 | 85 |

## ለውይይት የቀረበ(Brainstorming) ስትራቴጂክ እርምጃዎች

1. ለዋናው መ/ቤት የህንፃ ግንባታ ማካሄድ ፕሮጀክት፣
2. ከግለሰብ ለተከራዩ ቅ/ጽ/ቤቶች የህንፃ ግንባት ፕሮጀክት
3. የሰው ሃብት፣ ግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣ የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ዘመናዊ የማድረግ ፕሮጀክት፣
4. የዋናው መ/ቤት ጋራዥ ማስፋፊያ ፕሮጀክት፣
5. የቅ/ጽ/ቤቶች ኔት ወርክ ዝርጋታ የማጠናቀቅያ ፕሮጀክት፣
6. ለሠራተኞች የትራንስፖርት ሰርቪስ አገልግሎ የሚሰጡ አውቶብሶች ግዢ ፕሮጀክት፣
7. የተጀመረውን R.D.B.S ፕሮጀክት ማጠናቀቅ፣
8. የሊደር ሺፕና የሥራ አመራር ሥልጠና ፕሮጀክት ለዳይሬክተሮች፣ ለቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች የመስጠት ፕሮጀክት፣
9. የመሰረታዊ የኮምፒውተር አጠቃቀም ስልጠና ፕሮጀክት፣
10. የመ/ቤቱን ቤተ መፅሀፍትን በዘመናዊ መንገድ የማደራጀት ፕሮጀክት፣
11. የረጅም፣አጭርና የሥራ ላይ ሥልና ፕሮጀክት፣
12. ዘመናዊ የመረጃ መሠብሰቢያ መሣሪያዎች ግዥ ፕሮጀክት (GPS ,PDA ,UMPC,..)
13. High Resolution Satelight Imagery ( High resolution GIS software)
14. የተለያዩ አገሮች ልምድ ልውውጥ ፕሮጀክት፣
15. R.R.A( Rural Rapid Assessment) ፕሮጀክት
16. የፋይናንስ ማፈላለግ ፕሮጀክት፣
17. ለግብርና ቆጠራ የሚስፈልጉ ተጨማሪ ግብዓቶችን መጨመር ፕሮጀክት፣
18. የዶክመንቴሽን ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክት፣
19. የሚዲያ አጠቃቀም ማሻሻያ ፕሮጀክት፣
20. የስታቲስቲክስ መረጃ ጥቅም የሙያ መስገንዘቢያ የፅሁፍ ፕሮጀክት፣
21. የሰራተኞች የኮሚኒኬሽን አቅም ክህሎት ማሻሻያ ፕሮጀክት፣
22. የህትመት አገልግሎ የአውቶሜሽን ማሻሻያ ፕሮጀክት፣
23. የመረጃ ስርጭት ተደራሽነትና የተገልጋዮች ዕርካታ ማሻሻያ ፕሮጀክት፣
24. የቤተመፃህፍት የዶክመንቴሽን መረጃ ክምችት ፕሮጀክት፣
25. የሠራተኞች የባለድርሻ አካላትና የልማት አጋሮች የምስጋና ቀን ፕሮጀክት፣
26. የስነ-ምግባር ማሻሻያ ፕሮጀክት፣
27. በሥርዓተ ትምህርት የስታቲስቲክስ ግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮጀክት፣

28. የአደቢ.ኽርዋል መረጃ ዝግጅትና ክምችት ማሻሻያ ፕሮጀክት፣
29. የሀብት ማፈላለግ ፕሮጀክት፣
30. የባለ ድርሻ አካላት የልማት አጋሮች ማበረታቻ ፕሮጀክት፣
31. የሠራተኞች ማበረታቻ ፕሮጀክት፣
32. የመረጃ ጥራት ቁጥጥር ፍሬም ወርክ (EDQAF) ማዘጋጃ.ያ ፕሮጀክት፣
33. የስታቲስቲክስ ሕጉን ማሻሻያ ፕሮጀክት
34. የስታቲስቲክስ ቅ/ጽ/ቤቶችን በዋይድ ኤሪያ ኔት ወርክ (WAN) የማያያዝ ፕሮጀክት፣
35. ስታንዳርድ ፅንሰ-ሐሳቦችን፣ፍቺዎችን፣ኮዶችንና ምደባዎች ማዘጋጃ.ያ ፕሮጀክት፣
36. የመረጃ ቋት የማሻሻያ ፕሮጀክት፣
37. የሰራተኞች ዕውቀትና ክህሎት ማጎልበቻ ፕሮጀክት፣
38. በጂ.አ ስፓሻል ዳታ መልክ መረጃዎችን ለማውጣት የሚያስችል አጋዥ ፕሮጀክት፣
39. የስታቲስቲክስ ቢዝነስ ሬጅስተር ፕሮጀክት፣

# ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች

1. የህንፃ ግንባታ ማካሄድ ፕሮጀክት
2. የሰው ሀብት የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ዘመናዊ የማድረግ ፕሮጀክት
3. የዋናው መ/ቤት ጋራዥ ማስፋፊያ ፕሮጀክት
4. የቅ/ጽ/ቤቶች ኔት ወርክ ዝርጋታ የማጠናቀቂያ ፕሮጀክት
5. ለሠራተኞች የትራንስፖርት ሰርቪስ አገልግሎት ፕሮጀክት
6. የረጅም፣ የአጭር እና የሥራ ላይ ሥልጠና እንዲሁም በተለያዩ ሀገሮች የልምድ ልውውጥ በተለያዩ ፕሮጀክቶች ማካተት
7. የቤተ-መፅሐፍትና ዶክመንቴሽን መረጃ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮጀክቶች
8. ዘመናዊ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ግዥ በተለያዩ ፕሮጀክቶች ማካተት (GPS, PDA, UNPC, HR (High resolution Satellite imagery, GIS, ስካነር)
9. ለሚዲያ አጠቃቀም የማሻሻያ ጥናት ፕሮጀክት
10. የህትመት አገልግሎት ማሻሻያ በየፕሮጀክቱ የማካተት ፕሮጀክት
11. በሥርዓተ ትምህርት የስታቲስቲክስ ግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮጀክት
12. የስታቲስቲክስ ህጉን ማሻሻያ ፕሮጀክት
13. የመረጃ ቋት የማሻሻያ ፕሮጀክት
14. በጂኦ ስፓሻል ዳታ መልክ መረጃዎችን ለማውጣት የሚያስችሉ አጋዥ ፕሮጀክት
15. የአገሪቱን የመሬት ሽፋንና አጠቃቀም ፕሮጀክት
16. በኤሪያ ፍሬም የጥናት ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ፕሮጀክት
17. የስታቲስቲክስ መረጃ ጥራት ማረጋገጫ ሠነድ (EDQAF) ማዘጋጂያ ፕሮጀክት
18. የስታቲስቲክስ ቢዝነስ ሬጅስተር ፕሮጀክት
19. የስታቲስቲክስ ጥናቶች ፍሬም ወቅታዊ የማድረግ ፕሮጀክት